# C3G



## CONNECT TO: GLORIFY, GROW, GO

“እ ን ያ ያ ዝ”

ለማምለክ ለማደግ ለመሄድ

# “በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር” (ሐዋ 2፡42)።

**መዝሙረ ዳዊት**
**ለቤት ህብረቶች የተዘጋጀ**
**ሁለተኛው የጥናት መጽሐፍ**
**መዝሙረ ዳዊት**

ለቤት ህብረቶች የተዘጋጀ

# ሁለተኛው የጥናት መጽሐፍ

ይህ ጥናት የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ሁለተኛው ክፍል ነው። ከዚህ በታች ያለው የጥናቱ መግቢያ መልእክት ከመጀመሪያው መጽሐፍ ጥናት ጋር እጅግ ይመሳሰላል። ነገር ግን ጥያቄዎቹ ልዩነት ስላላቸው ጥያቄዎቹን ተወያዩ።

መዝሙረ ዳዊት ከብሉይ ኪዳን 39 መጽሐፍት አንዱ ሲሆን 150 ምዕራፎች ያሉትና **ዳዊትን ጨምሮ ሌሎችም ዘማሪዎች የዘመሩዋቸው የመዝሙሮች ስብስብ ነው።** ከ1000 በላይ በሆኑ ዓመታት የተደረሰ ሲሆን ስለ እግዚአብሔር ህልውና በግልጽ የሚያስረዳ፣ የእግዚአብሔርን ባህርይ የሚያስተምር፣ብዙ ባህልና ታሪክን ያካተተ፣ ክፉዎችንና ጻድቃንን የሚያነጻጽር፣ የሰዎችን የህይወት ገጠመኞችን የሚያንጸባርቅ፣ የማህበረሰብና የግለሰቦችን እውነተኛ የነፍስ ጩኸት፣ጸሎት፣ድል.፣ ደስታና ሀዘን የሚገልጥ፣ **ስለክርስቶስ ትንቢታዊ መልዕክት የያዘ**፣ለእግዚአብሔር የመታዘዝና ያለመታዘዝ ውጤት በግልጽ የሚናገር መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ተምሳሌታዊ ንግግሮችንም በብዙ ይጠቀማል።በዚህ መጽሐፍ ያሉ መዝሙሮች በሙዚቃ መሣሪዎች ታጅበው የተዘመሩ መዝሙሮች ናቸው። በተለይም የእስራኤላውያንን ወይም የአይሁዳውያንን በግልም ይሁን በማህበረሰብ ከምርኮ በፊት፣በምርኮ ጊዜና ከምርኮ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ህብረት ይናገራል።

በመዝሙር መጽሐፍ የተጻፉ መዝሙሮች በጸኃፊው ዘመን የተጻፉና የተዘመሩ መዝሙሮች ብቻ ሳይሆን በኋላም በነበሩት ዘመናት የተዘመሩ መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም። መዝሙር አሁንም እንደምንዘምረው ሆኖ እንደተቀመጠም ማወቅ አለብን።

ይህ የመዝሙር መጽሐፍ በአምስት ትንንሽ መጽሐፍት ይከፈላል (የአምስቱም) መደምደሚያቸው አንድ ዓይነት መልክ አለው፡፡

1. 1-41=41 መዝሙሮች (ለምሳሌ መዝጊያ ቁጥር 41፡13 "ከዘላለም እስከ ዘላለም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ። አሜን አሜን")።
2. መዝሙር 42-72=31 መዝሙሮች (ለምሳሌ መዝጊያ ቁጥር 72 ፡19-20፡- ቁ.19 የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይሙላ። ይሁን ይሁን)።
3. መዝሙር 73-89=17 መዝሙሮች (ለምሳሌ መዝጊያ ቁጥር 89፡52 "እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ ይሁን ይሁን")
4. መዝሙር 90-106=17 መዝሙሮች ናቸው መዝ (106)፡48 መደምደሚያ ነው።
5. መዝሙር 107-150=44 መዝሙሮች ናቸው (መዝሙር 150 እንዳለ እንደ መዝጊያ ይቆጠራል)።

በተጨማሪም መዝሙሮቹ የተለያዩ ዓይነት መዝሙሮችና በብዛት በሙዚቃ የተሰሩ ናቸው። ለምሳሌ የጥበብ፣ የምስጋና፣የተለያዩ ጸሎቶች፣የአምልኮ፣የመሢህ፣የጽዮን፣የመርገም፣የንጉስ፣የቤተ መቅደስ እና ወዘተ ናቸው። በጥቅሉ እንጂ አንዳንዶቹ ተደራራቢ መሆናቸው ይታወቃል። እነዚህ በዚህ ጥናት ሰፋ ባለ መልኩ የምናያቸው ይሆናል። መዝሙሮቹን የበለጠ ለመረዳት የስንኞችን ማለትም አንደኛና ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መስመር እንዴት እንደሚስማማ፣ እንደሚነጻጸር፣ እንደሚደራጅና ሌሎችንም ማየቱ ጥሩ ይሆናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔዎች እንደ አማርኛ የመጨረሻ ፊደልና የሀሳብ አንድነት ሳይሆን የሚገጥመው የሁለቱና ከዚያም በላይ ስንኞች የሀሳብ አንድነትና ለአንዳንዶቹ የመጀመሪያ ፊደላት መግጠም ይሆናል። በርግጥ የአነባብ ውበት ለሁሉም ይጠቅማል።

በቤተክርስቲያናችን ይህን ጥናት ሲዘጋጅ አጠቃላይ ዓላማው ስለ መዝሙረ ዳዊት የተሻለ እውቀት በማግኘት በየቀኑ በምንኖረው ኑሮ ቅኔውን (**ግጥሙን**) ውዳሴውን ጸሎቱንና ሌሎቹንም የአጻጻፍ ዘይቤዎችን በመጠቀም ህይወታችንና አገልግሎታችንን እንድናጎለብት ነው። ለብዙ አማኞችም በረከት እንዲሆን ጸሎቷ ነው። መሪውም ይሁን ህብረቱ **ጥያቄዎችን ትኩረት እየሰጣችሁ እንብቡት።**

የቤተ ክርስቲያንቷ ትምህርት ክፍል 214-703-0100 (ext 217)

**ዛሬ ከመግቢያው ጥያቄዎችን የመወያያና ወደ ፊት ላለን የጥናት ጊዜያት የጸሎት ቀን ይሆናል**

1. ከመጀመሪያ መጽሐፍ ማለትም ከጥናት አንድ በአጭሩ ምን እንደተማራችሁ አካፍሉ?
2. በዚህ ጥናት በ5ኛው የመወያያ ጥያቄ መሠረት ምን እንቅስቃሴ አደረጋችሁ? መስክሩ? ካልሆነ አምስተኛውን ጥያቄ ተወያዩ።
3. እስካሁን ስለ መዝሙረ ዳዊት ምን ትምህርት አገኛችሁ?
4. ቤተክርስቲያን ይህን ጥናት ማዘጋጀት ለምን አስፈለጋት?
5. ቡድናችሁ ተጨማሪ ሰው የሚያስፈልገው ከሆነ ሰው ለመጨመር ተወያዩ። (እያንዳንዳችን አንድ አንድ ሰው መምጣት ከቻልን ጥሩ ይሆናል):: በመካከላችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመምራት ለማገልገል የሚትፈልጉ በመሪያችሁ በኩል ትምህርት ክፍሉን ማነጋገር ትችላላችሁ።

ምስጋና፡- ስለ ትጋታችሁ ማለትም በወር አንዱን ቀን የጸሎት ቀን ስላደረጋችሁ እና ጥናቱን በትክክል እያጠናችሁ ስላላችሁ ጌታ ይባርካችሁ።

ስለ እናንተ ሁል ጊዜ ከመጸለይ አንቆጠብም!

# ጥናት 16

# የንባብ ክፍል መዝሙር (15)

የመዝሙር መጽሐፍ በተቀደሰና ጌታን በሚያስከብር ህይወት ስለ መኖር ምን ያስተምራል

ርዕስ፦ **በእግዚአሔር ክብር ማደሪያ ድንኳን በተቀደሰው ተራራ መኖር**

***መግቢያ***

*መዝሙር 15 የቤተ መቅደስ መዝሙር ተብሎ ከሚመደቡት መዝሙራት መካከል የሚካተት መዝሙር እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። የዚህ መዝሙር ደራሲ ወይንም ጸሐፊው መዝሙረኛው ዳዊት ነው። ዳዊት የእግዚአብሔርን ህዝብ በቅድስና እና በጽድቅ ህይወት ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ወደ መገኘቱ እና ወደ ማደሪያው ሊመጣ እንደሚገባው ያስገነዝባል። በመጨመርም የእግዚአብሔር ህዝብ በቅድስና እና በጽድቅ በማደሪያው መመላለስ እንድሚገባ ያስተምራል። ስለዚህም ከዚህ ክፍል የምንገነዘበው የእግዚአብሔር ህዝብ ዝም ብሎ እንደመሰለው እና በዘፈቀደ የሚኖር እና የሚመላለስ መሆን እንደሌለበት ነው። መዝሙረኛው በዚህ ክፍል እንደሚያስተምረን ዋናው ጉዳይ በቤቱ በቅድስና በጽድቅ እንድንመላለስ ማስተማር ሲሆን አያይዞም ሁሌም በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ እዴት እንደምንኖርና እና እንዴት እንደምንመላለስ ያስተምረናል። ወደ ኤፌሶን ሰዎች ከምዕራፍ 4-6 በጌታ ቤት እንዴት መኖር እንዳለብን ያስተምራል። 1ጴጥ 1 በጽድቅ እንዲንኖር ያስተምራል። አካሄዳችንና ባህሪያችንንም በጥንቃቄ መጠበቅ እንዳለበት ያስተምራል። በቃል እና በአደበታችን በእግዚአብሔር መገኘት መጠንቀቅ እንዳለብን ጥበብን ያስተምረናል። በአዲስ ኪዳን የጌታ መንፈስ መገኘት በሁሉ ቦታ ነው።*

***ዓላማው***

*በዚህ ጥናት የእግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ ጽድቅን እና እውነትን ስለሚወድ በጽድቅ እና በቅድስና ከአምላካችን ጋር መራመድ እና በዚህ ህይወት እንድናድግ እና እንድንሰፋ ለማስገንዘብ ነው።*

1. ***በጌታ ቤት ማን ያድራል … ማንስ ይኖራል?***

***ቁ, 1 ሀ. አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል?*** *መዝሙረኛው በዚህ ቁጥር የመጀመሪያው ክፍል የሚያነሳው ጥያቄ እጅግ በጣም ወሳኝ እና ቁልፍ ሃሳብ ነው፡ ለእንግድነት ወይንም ለጊዜው ጉብኝት ሳይሆን በመገኘቱ ውስጥ (መሆንን) የሚያመለክት ሃሳብን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚህ ቀደም የሆነውን የኖርነውን ህይወት አሮጌ እንደሆነ በመጥቀስ ጌታን ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ የሆነልንን አዲስ ህይወት እንዳለ ያበስረናል። ከዚህም ህይወት ጋር ተያይዞ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን የተመረጠ ትውልድ የንጉስ ካህናት ቅዱስ ህዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ እያለ በሌላም ክፍል ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው። የሆነልንን ሳይሆን የሆነውን ያመለክተናል (1ጴጥ 2፡9, 2ቆሮ 5፡17)።*

***ቁ.1 ለ. በተቀደሰው ተራራህ ማን ይኖራል?*** በዚሁ ቁጥር የመጀመሪያው ክፍል ከተጠቀሰው የእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ከመሆን ሊያወጡን የሚችሉ ብዙ ጉዳዮች አይጠፉም። ስለዚህ ይህ ክፍል ደግሞ በመገኘቱ ውስጥ ለመሰንበት እና በመገኘቱ ውስጥ (መኖርን) የሚያመለክት ሃሳብ ነው። በአዲስ ኪዳንም በክርስትና ህይወታችን መንፈሳዊ ፍሬን ማፍራት የምንችልበት በጌታ መሆናችን ሚስጢር እንደሆነ ያስተምራል፡ አያይዞም በዚህ የሆነልን ህይወት ደግሞ መኖር እንዳለብንም ያስተምራል። በሌላ አባባል ቀዳሚው ጉዳይ ቅርንጫፍ መሆኑ ሲሆን፡ ቀጣዩ ጉዳይ ደግሞ ቅርንጫፉ በወይኑ ግንድ ላይ ተጣብቆ መኖሩ የህልውናው ቁልፍ ሚስጢር እንደሆነም መዘንጋት የለበትም። ቅርንጭፍ ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል እንዲሁ እኛም በጌታ (በሆነልን) ህይወት (ባንኖር) በራሳችን አንዳችም ነገር ልናደርግ አንችልም። ስለዚህ የጌታም ጥሪ እኔ የወይኑ ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎቼ ናችሁ በእኔ ኑሩ የሚል ነው (ዮሐ 15፡3-5)።

2. ***አንድ የእግዚአብሔር ሰው በጌታ ቤት በጥሩ ህብረት ለመኖር ምን ማድረግ አለበት?***

**ቁ. 2 *ሀ*. በቅንነት የሚሄድ (upright)**

*በቁጥር አንድ ላይ ለተነሱት ጥያቄዎች ክፍሉ በሚቀጥሉት ቁጥሮች መልስ ይሰጣል። በመጀመሪያም በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ የሚሆን እና የሚኖርን ሰው አካሄዱ በቅንነት መሆኑን ያመለክታል። ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎል እና አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታል (ዘፍ 5፡24)። ዛካርያስና ባለቤቱ ኤልሳቤጥና በጌታ ቤት ያለ ነቀፋ ያገለግሉ ነበር (ሉቃ 1፡6)። በየትኛውም አይነት ጎዳና አካሄዳችን በእግዚአብሔር ፊት ስለሆነ በቅንነት ለመሆናችን እጅግ ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል። በአስተሳሰባችና በተጋባራችን በቀና መንገግ ልንጓዝ ያስፈልጋል።*

**ቁ.2 ለ. ጽድቅን የሚያደርግ፡-**

*ይህ ሃሳብ ስለ ጽድቅ የሆነውንና ያልሆነውን ጉዳይ ለይቶ ስለማወቅ ብቻ ሳይሆን ጽድቅ እንደሆነ የተረዳነውን እና ያወቅነውን ያንን ስለማድረግና ስለመፈጸም የሚናገር ሃሳብ ነው። ጌታ ወደ አጥማቂው ዮሐንስ በመጣ ጊዜ ይህንን አንተ ልታደርግ አገባህም ባለው ጊዜ የለም ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባኛል ብሎ መልሶለታል (ማቴ 3፡15 የሐ 10፡34-35)። እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልሁ። ማወቅ አንድ ነገር ነው ያወቅነውን እርሱን መፈጸም ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው።*

**ቁ.2. ሐ. በልቡም እውነትን የሚናገር፡-**

*የልባችን ሃሳብ እና የአንደበታችን ቃል የታረቀ መሆን እንደሚገባው ያመለክታል። በአንደበታችን የምንናገረው ሃሳብ በልባችን ውስጥ ካለው ሃሳብ ጋር ተቃራኒውን ሊሆን የሚችልበት አጋጣም አይጠፋምና በአንደበታችን ከመውጣቱ በፊት ሀሳቡ የሚጠነሰስበት በልባችን ስለሆነ በልባችን ያለው ጉዳይ እውነተኛ መሆኑን እርግጠኞች መሆን አለብን። "አቤቱ፥ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን" (መዝ 19፡14)። እነዚህ ሁለቱ ነገሮች እንድስማሙለት ልቡን የሚመረምረውን ጌታን ሲጠይቅ እንመለከታለን።*

**ቁ. 3. *ሀ*. በአንደበቱ የማይሸነግል"፡-**

*ብዙ ጊዜ አንደበት በልባችን ያለውንና የሞላውን ነገር እንደሚገልጥ የተወቀ ነው። አንዳንዴ ግን በልባችን ያለውን ክፋት ለመሸፈኛ አንደበታችን የሽንገላ ቃላትን ሊጠቀም መቻሉ አያጠያይቅም፡፡ ምሳ 24፡2 እንደሚከተለው ይላል "ልባቸው ግፍን ታስባለችና ከንፈራቸውም ሽንገላን ትናገራለች" እንድሁም መዝ 34፡13 "አንደበትህን ከክፉ ከልክል ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ" ይላል። እውነትንና ውሸትን መናገር ጌታ አይወድም። ሰዎች እኛን ቢሸነግሉ እንደማንወድ እኛም ሌሎችን መሸንገል የለብንም።*

**ቁ. 3 . ለ. በባልጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ፡-**

*ዘመዶቹንም የማይሰድብ፣ በእግዚአብሔር ድንኳን የሚያድር በተቀደሰው ተራራው የሚኖር ሰው ከሌላው ሰው ጋር ባለው ግንኙነት ከክፋት በመራቅ ጽድቅን በመኖርና በማድረግ መሆን እንዳለበት ያሳያል። የቅርብ የሆኑን ሰዎች በትህትና እና በአክብሮት ግንኙነቶቻችንን የማንከታተል ሲሆን በቀላሉ ልናሳዝናቸው እና ልንጎዳቸው እንችላለን። ስለዚህ መኖሪያው በእግዚአብሔር መገኘት ያደረገ ሰው በቅርቡ ላሉት ወዳጆች የበለጠ መጠንቀቅ እንዳለበት ያሳስባል። ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ታላቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶናል።*

**ቁ.4. *ሀ*. ኃጢያተኛ በፊቱ የተናቀ**

*በእግዚአብሔር ማደሪያ ሊኖር የሚፈልገ ሰው አንዱ ሊጠነቀቅ የሚገባው ጉዳይ ከኃጢያተኛ ባልንጀራ የሚመጣውን የኃጢአት ግብዣ ሊያታልለው አይገባም። ኃጢአት የማያጓጓው መሆን አለበት። መዝ1፡ 1 "ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢያተኞችም መንገድ ያልቆም በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ" በማለት ከኃጢያተኞች ሰዎች ለጽድቅ ህይወትና አዳሄድ እንቅፋት እና ተጽዖኖ ሊደረግ እደሚችል ያመለክታል። እዚህ ጋር መታሰብ ያለበት ኃጢያታቸውን*

እንጂ ሰዎቹን መጥላትን እንዳልሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ጌታም ኃጢያትን እስከ ሞት ድረስ ጠልቶ ነገር ግን ኃጢያተኛውን እስከ ሞት ድረስ እንደ ወደደው አንዘንጋ።

**ቁ.4. ለ. እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር**

በእግዚአብሔር ቤት ለመኖር የወሰነ ሰው ቤተሰቡን መውደድ ግዴታው ጭምር መሆኑ ሊታወቅ የሚገባ ነው። ከኃጢያተኞች ጫና እና ተጽዖኖ ይልቅ እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ሰዎች አካሄድና ህይወት የምንማረውና የምንጠቀውም የበለጠ ስለሆነ እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ሰዎች ህይወት አክብሮት ልንሰጥ ያስፈልገናል። "ኃጢያተኛ ዘይትን ከሚቀባኝ ይልቅ ጻድቅ በምህረት ቢገስጸኝ ይበልጣል ይለናል" (መዝ 141፡5)።

**ቁ.4. ሐ. ለባርንጀራው የሚምል የማይከዳም፡-**

በእግዚአብሔር ማደሪያ የሚኖር ሰው ለወዳጆቹ የቃል ኪዳን ሰው ሊሆን እንደሚገባ ያሳያል፣ እንዲሁም ቃሉንም በመጠበቅና በመፈጽም የሚታወቅ ሰው ሊሆን እንደሚገባው ያመለክታል፡፡ ጌታ በቃሉ እውነተኛ ነው።

**ቁ.5.ሀ. ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፣**

የእግዚአብሔር ሰው ሀብትን የሚያገኘውና የሚያከማቸው በሌሎች ጉዳትና ጉድለት መሆን እንደሌለበት ያሳስባል። ይልቁንም ከሌሎች ጋር በጽቅድ አካሄዱና ግንኙነት ሳቢያ በድካሙ ከሚያገኘው ትርፍ ይልቅ በአቆራጭ የሚገኝን ሀብት የማይሻ ሊሆን ይገባል። ዕብ 13፡5 አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለመውደድ ይሁን በማለት ሲመክረን ገንዘብን መውደድ ደግሞ የክፋት ሁሉ ስር መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ጢሞ 6፡10 ይገልጻዋል።

**ቁ. 5. ለ. በንጹህ ላይ መማለጃን የማይሻ፣**

የጻድቅ ሰው አካሄዱ በእውነት እና በቅንነት ስለሆነ የእግዚአብሔርም ማደሪያ የጽድቅና የቅንነት ማደሪያ በመሆኑ በተለያየ መንገድ ማማለጃ መፈለግ ከበረከት ያጎድላል። ዋጋ ቢያስከፍልም ከእውነት ጋር በመስማማት ሊቆም እንደሚገባው ያመለክታል። ልሥጋዊ ጥቅም ነፍስን ማሳዘንና ማጣት ዋጋ የለውም።

**3. ውጤት**

**ቁ. 5. እንዲህም የሚያደርግ ለዘለዓለም አይታወክም**

በመጀመሪያው ቁጥር ላያ ለተነሱት ጥያቄዎች ዘማሪው መልስ ይሆናሉ ያላቸው እውነታዎች በዝርዝር ካቀረበ በኃላ፣ በመደምደሚያው ላይ እነዚህም የተዘረዘሩትን የጽድቅ አካሄዶችን የሚሄድ ሰው ወይንም በጽድቅ ህይወት የሚኖር ሰው በእግዚአብሔር ማደሪያ ሲኖር በመቅደሱ ሲያመልክ በአደባዮቹ ሲመላለስ በድንኳኑ ሲያድር የሚያናውጠው ነገር እንደሌለ በእርግጠኛነት ተናግሮ ይደመድመዋል። እግዚአብሔር አካሄዳቸው እንደጸናላቸው እንደማይናወጥ ጻድቃን ሰዎች ያርገን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. የማደሪያው ድንኳንና የመገናኛው ድንኳን በተመለከት እስከ አሁን ያለህን መረዳት አካፍል? አጥጋቢ ካልመሰላችሁ የሚቀጥሉትን ጥቅሶች አንብባችሁ የተረዳችሁትን ተነጋገሩበት? **(ዘሌ 9፡23 ዘሌ 10፡9)**
2. በቁ. 1.ሀ. በድንኳንህ የሚለው ምንን ለመግለጽ ነው ትላለህ?
3. በቁ.1.ለ. የተቀደሰው ተራራ የሚለውስ ሃሳብ ምንን ለመግለጽ ነው ? ተራራስ በራሱ የተቀደሰ ይሆናል ማለት ነው? ኢሳ 57፡13, ኢሳ 11፡9
4. በቁ.1 መሰረት ያድራል ይኖራል የሚሉት ሀረጎች ወይንም አባባሎች ከክፍሉ አንጻር እንዴት ትረዳዋለህ? መዝ 91፡1 , ራዕ 21፡3 ዘዳ 33፡12, 28,
5. አዲስ ኪዳን በ2ኛ ቆሮ 6 እና በ1ኛ ቆሮ 3 የእግዚአሔር ቤተ መቅደስ የእግዚአሔር ማደሪያ ወይንም ድንኳን በምን እንደተተካ ያስተምረናል?

6. ቁ.2. በቅንነትና በጽድቅ የሚሄድ በልቡ እውነትን መናገር ማለት ምንድነው? ቅን ማለትን በራስህ አባባል አስረዳ? ሉቃ 1፡6 ምሳ 21፡3 ማቴ 3፡15
7. ቁ.3.ሀ. በአንደበቱ የማይሸነግል፣ ምን አይነት ሰው ነው? አንደበቱ እንጂ ትክክል ነው ማለት ነው? መዝ 34፡12-13 መዝ 120፡2

   ቁ. 3. ሐ. ባልጀራውን የይበድል፡ ዘመዶቹንም የማይሰድብ፣ የሚለውን እንዴት ትረዳዋለህ? አንዳዴም ቢሆን ከባልጀራ እና ከገዛ ዘመዶች ጋር በትህትና በመከባበር የሚቸግረው ለምንድነው ትላለህ? ማቴ 10፡36 ማቴ 13፡57 በግልጽ ተነጋገሩበት።
8. ቁ.4. ሀ. ኃጢያተኛ የሆነውን ሰው መናቅ ይኖርበታል ማለት ነው? በኃጢያቱና በሰውዬው መካከል እንዴት ነው ለይቶ ማየት የሚቻለው? እግዚአሔር ልጁ እስኪሞት ድረስ ኃጢያትን ጠልቶል በአንጻሩም ኃጢያተኛው ለማዳን ደግሞ አንድያ ልጁን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶል።

   ቁ.4.ለ. እግዚአሔርንም የሚፈሩትን ማክበር ማለት እንዴት ነው? ዕብ 13፡7

   ቁ.4.ሐ. ለባልጀራው የሚምል፡ የማይከዳም፣ የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ? በእግዚአሔር ቃል ውስጥ በመደጋገም በሰው ልጆች መካከል ስለለው ወዳጅነት መጠቀሱ ለምን ይመስልሃል? ወዳጃችንስ ማነው? ሉቃ 10፡30-36
9. ቁ. 5.ሀ. በአራጣ የማያበድር ማለት ምን ማለት ነው? በራስ አባባል ግለጸው። ከማጠቃለላችሁ በፉት በማስጠኛው ላይ ያለውን ሃሳብ ተመለከቱት።

   ቁ.5.ለ. በንጹህ ላይ መማለጃን መቀበል ማለት ምንድነው? የሚረዳ ከሆነ ማስጠኛውን  ተመልከቱት።
10. ከቁ. 2-5 በእግዚአሔር ድንኮን የሚያድርና የሚኖር ሰው ሊኖሩት ስለሚገባው ባህሪያት ሰብሰብ አርጋችሁ ጥቅሶቸው? ወደ 10 ባህሪያት ተጠቅሰዋል።
11. የ10 ነገሮች ውጤቱ ወይም የተሰጠው ተስፋስ ምንድነው?
12. ከመዝ 15 አጠቃላይ ምን ተማራችሁ?

***መደምደሚያ፡-***

መዝ 15 በ5ቱም ቁጥሮች እግዚአብሔርን የሚያምን ሰው በጌታ ማደሪያ ቤት እንዴት መሮር እንዳለበት በጥብቅ ያስተምራል። አማኝ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እርሱም እንዲቀድስ ተጠርቷል ።

ዘሌ 11፥44እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ሰውነታችሁን ቀድሱ፥ ቅዱሳንም ሁኑ፥ እኔ ቅዱስ ነኝና በምድርም ላይ በሚሳብ ተንቀሳቃሽ ሁሉ ሰውነታችሁን አታርክሱ።

ዘሌ 11፥45 እኔ አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር ነኝ እንግዲህ እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።

ዘሌ 19፥2 እስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ በላቸው፡- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።

ዘሌ 20፥26 እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና፥ ለእኔም ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ ለይቻችኋለሁና ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ።

ዘሌ 21፥8 የአምላክህን እንጀራ ያቀርባልና ስለዚህ ትቀድሰዋለህ እኔም የምቀድሳችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እርሱ ቅዱስ ይሁንልህ።

1፥15-16 ዳሩ ግን። እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ (1ጴጥ)። እንዲሁም ኤፌ 4-6 ሮሜ 12-16 ሌሎችም መልዕክቶች ተቀድሰን እንዲድንኖር ያስተምራል።

# ጥናት 17
## *መዝሙረ ዳዊት*
## *ምዕራፍ* 73
## *ይህ ጥናት የሁለት ቀን ቢሆን ይመረጣል*

***መግቢያ፡-***

*መዝሙር* 73 *የጥበብ መዝሙራት ተብለው ከሚመደቡት መካከል አንዱ ሲሆን የመዝሙረ ዳዊት ሦስተኛ ክፍል (መጽሐፍ ሦስት) ከፋች ምዕራፍ ነው። ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው፣ የጥበብ መዝሙራት አብይ አላማ እግዚአብሔርን የመፍራት እና ወደ እርሱ የመቅረብን መልካምነት፣ እንዲሁም የኃጢአት ሕይወትን ከንቱነት በማስጨበት የእግዚአብሔር ሰዎች በጽድቅ እና እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩ የሚያበረታቱ መዝሙሮች ናቸው።*

*በዚህ መስረት መዝሙር* 73 *ዘማሪው በዚህ መዝሙር ውስጥ የኃጢአተኞችን ሕይወት እና ስኬት ፈታኝ መሆኑን እንዲሁም ስለ ጽድቅ ብሎ መከራ ለሚቀበለው አማኝ የሚያስጎመጅ መሆኑን ከራሱ ገጠመኝ/ ልምድ በመነሳት ያስረዳል። ሆኖም ግን የኃጢአተኞች ሕይወት ምንም የስኬት ቢመስል እና ቢፈትንም ጊዜያዊ እና እግዚአብሔር በጊዜው የሚፈርድበት ሕይወት መሆኑን በማስገንዘብ፣ ዘማሪው በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ እና ፈተና ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እና እርሱን መከተል የሚያዋጣ መሆኑን ያስገነዝባል።*

*በመዝሙር መግቢያ የተጠቀሰው "አሳፍ" የሚል ስም ከቤተ መቅደስ አገልጋዮች/ዘማሪዎች/ አንዱ ሲሆን እርሱም የሌዊ ዘር ነው።*

*የጥናቱ ዓላማ፡-*

*ይህ ጥናት በዚህ ምድር ጌታን ያላመኑ ሰዎች ባላቸው ጊዜያዊ ስኬት አማኞች እነርሱን በማየት በሚጠፋ ነገር እንዳይፈተኑ ለማበረታታት እና ጸንተው ወደ ጌታ መቅረብ አማራጭ የሌለ ነገር እንደሆነ ማሳወቅ።*

***መዝ* 73 *እንደሚከተለው ከፍለን ልናጠናው እንችላለን* ፡-**

I. *መንደርደሪያ* - *የማይካድ እውነት- ለሚከተሉትና ልባቸው ለቀና እግዚአብሔር ቸር ነው* (1-3)
II. *የከፉዎች ጊዜያዊ ስኬት እና ፈታኝነት* (4-17)
III. *በከፉዎች ላይ የእግዚአብሔር ፍትሐዊ ፍርድ* (18-20)
IV. *መደምደሚያ* - *በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መልካምነት* (21-28)

*ሀ. መንደርደሪያ፡- የማይካድ እውነት-ለሚከተሉትና ልባቸው ለቀና እግዚአብሔር ቸር ነው* **(*መዝ* 73፡1-3)**

*በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች ውስጥ ዘማሪው ቀጥሎ ላለው ክፍል ጥሩ መንደርደሪያ ይዘረጋል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር* ***<u>በእርግጥ ለልበ-ቀናዎች መልካም እና ቸር መሆኑን አስረግጦ</u>*** *ይናገራል። በአማርኛ ትርጉሞች ላይ በግልጽ ባይጻፍም ሌሎች ትርጉሞች ሲጀምሩ "በእግርጥ" እግዚአብሔር ልባቸው ለቀና ለእስራኤላዊያን ቸር ነው! በማለት ነው። በእርግጥ የሚለው ቃል የሚያስገነዝበን በምንም አይነት መልኩ ልባቸው ቀና ለሆኑ ሕዝቦቹ እግዚአብሔር መልካም መሆኑ ጥርጣሬ ላይ ሊወድቅ ፈጽሞ እንደማይገባ ነው። ሆኖም ግን ዘማሪው ይህንን እውነት ዘንግቶ እግዚአብሔርን ከሚከተልበት መንገድ ሊወድቅ እና ሊሰናከል ጥቂት ቀርቶት እንደነበረ ይመሰክራል ( ቁ.* 2)*። እግዚአብሔር ቸር የመሆኑ እውነት የማይጠየቅ ቢሆንም ይህንን እውነት ግን እንዲጠረጥር ያደረገው ነገር እንደነበረ ያስረዳል። በ ቁ.* 3 *ላይ እንደሚነግረን የእግዚአብሔርን ቸርነት ሊጠረጥር እና ከመንገዱ ሊወጣ የነበረው "የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና" ሲል ያስረዳል። የኃጢአተኞች እና የከፉዎች ሕይወት እየተሳካ ሲታይ እና በሌላው በኩል እግዚአብሔርን በጽድቅ እና በቅንነት የሚከተሉት በመከራ ሲያልፉ ሲታይ በእርግጥ ሰው እግዚአብሔር መልካም መሆኑን እንዲጠረጥር እንዲሁም እግዚአብሔርን መከተል የሚያዋጣ መሆኑን እንዲዘነጋ ሊያደርገው ይችላል። ዘማሪውም ከራሱ ሕይወት በመነሳት*

የሚመሰክረው ይሄንኑ ነው። "እግዚአብሔር ለሕዝቡ ቸር ነው እኔ ግን የኃጢአተኞችን ሕይወት አይቼ ከእግዚአብሔር መንገድ ልወጣ ትንሽ ነበር የቀረኝ!" ይላል። ዛሬም አማኞች በእንደዚህ ዓይነት ፈተና በየቀኑ እንደሚያልፉ የታወቀ እውነት ነው።

## ለ. የክፉዎች ጊዜያዊ ስኬት እና ፈታኝነት (መዝ 73፡4-17)

***መዝ* 73፡4-17** ባለው ዘማሪው በክፉዎች ሕይወት ውስጥ የታዘበውን ስኬት እና እንዴት እንደተፈታተነው ያስረዳል። ሆኖም ግን ዘማሪው ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ሲመጣ እና ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ ይህ ሁሉ ስኬት ጊዜያዊ መሆኑን ይገነዘባል። ከቁ. 4-12 የኃጢአተኞችን ስኬት በሚያስገርም አይነት መልኩ ይዘረዝራል። እነዚህ ሰዎች እንደ ሌላው ሰው ሁሉ የኑሮ ጣር እና ጣጣ የለባቸውም፣ በዘማሪው አመለካከት ለእነርሱ ነገር ሁሉ አልጋ በአልጋ ነው (ቁ 4-5 እንዲሁም 12)። ዓይናቸው የሰባ (ቁ.7)፣ ሃብታቸው የበዛ (ቁ. 12) ነው። ልባቸው ግን በትዕቢት የተሞላ (ቁ. 6)፣ አፋቸውን በሰማይና በምድር (በእግዚአብሔር እና በሰው) ላይ የሚናገሩ (ቁ 8 እና 9)ናቸው። እንዲያውም እግዚአብሔርን ባለመፍራት የሚኖሩት ኑሮ ስኬትን ስላስገኘላቸው እግዚአብሔር ከቶ የማያይ እና ድርጊታቸውን የማያውቅ እየመሰላቸው "እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልስ ዘንድ በውኑ እውቀት አለ?" በማለት ይዘብታሉ (ቁ. 12)። እንደዚህ ክፉዎች ለራሳቸው እግዚአብሔርን አለመፍራታቸው ብቻ ሳይሆን የእነርሱን ስኬት አይቶ የሚከተላቸው ሕዝብም አላቸው (ቁ. 10 አዲሱ መደበኛ ትርጉም ያነጻጽሩ)።

በቁ. 13 እና 14 ላይ ዘማሪው ይህ የኃጢአተኞች ስኬት እንዴት እንደተፈታተነው ያስረዳል። ክፉ ሰዎች ኑሮ እየቀለላቸው እና እየተሳካላቸው ሲሄዱ ሲያይ ዘማሪው **"ለካ ልቤን ንጹሕ ያደረግሁት በከንቱ ነው፣ እጄንም በየዋሕነት የታጠብኩት በከንቱ ኖሮአል" እንዲል አድርጎታል** (ቁ. 13 አዲሱ መደበኛ ትርጉም)። የራሱን ሕይወት ግን ሲመለከት ስለ ጽድቅ እና ስለ እግዚአብሔር እውነት ሁልጊዜ ጠዋት እና ማታ መከራንና ስድብን እየተቀበለ ነው የሚኖረው። እግዚአብሔር ኃጢአተኞች ሲሳካላቸው ዝም የሚል ከሆነና፣ ጻድቁን ከመከራ የማይስጥል ከሆነ፣ስለ እግዚአብሔር መከራ የምቀበለው እና የምሰደበው እንዲያው በከንቱ ነው ይላል (ቁ 14)። በእርግጥም ጌታን የሚወዱ ሰዎች በመከራ ሲንገላቱ፣ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች ደግሞ ሞልቶላቸው ሲታይ፣ እግዚአብሔን መፍራት ትርጉም የሌለው የሚመስልበት ጊዜ ብዙ ነው። ለምሳሌ ዕንባቆም 1፡1-4 ያለውን ይመልከቱ። በዚህ ክፍል ዘማሪውም እንደ ዕንባቆም ጥያቄ እንዲፈጥርበት የሚያደርገው ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ኃጢአተኛው ይለመልማል ጻድቁ ግን በመከራ ይኖራል። **ታዲያ እግዚአብሔርን መከተል በእርግጥ ትርጉም አለውን?**

ዘማሪው ከቁ. 15-17 ባለው ክፍል ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ሲመጣ እና ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ ያገኘውን መልስ ያስረዳል። በቁ.15 ላይ ከላይ እንደገለጸው የኃጢአተኞችን መንገድ መከተል ያዋጣል ብሎ ቢል እና መንገዳቸውን ቢከተል ኖሮ እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ጭምር ነበር የሚበድለው። ሆኖም ግን መንገዳቸውን አልተከተለም። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ሰዎች መከራን እየተቀበሉ ኃጢአተኞች እየተሳካላቸው የመሄዱ ምስጢር ለመረዳት እጅግ የሚያስቸግር መሆኑ ግልጽ ቢሆንም (ቁ 16)፣ ዘማሪው ለኃጢአት እጅ አልሰጠም። በቁ 17 ላይ እንደምንመለከተው፣ ዘማሪው ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲመጣ እና እግዚአብሔርን ሲፈልግ፣ ምስጢር ለሆነበት ነገር መልስን እዳገኘ እናያለን። ምንም እንኳ የሕይወት ዘይቤአቸው ፈታኝ እና አሰናካይ ቢመስልም፣ ዘማሪው ያስተዋለው ነገር ለካ ለምልመው እና ፈክተው ይታዩ የነበሩት ኃጣን እግዚአብሔር ፍጻሜን እንዳበጀላቸው ነው።

## ሐ. በክፉዎች ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ (መዝ 73፡ 18-20)

መዝ 73፡ 18-20 ባለው ክፍል አንድ ጊዜ ስኬታማ የነበሩት፣ ለሚመለከታቸው ገናና እና አስፈሪ የነበሩትን እግዚአብሔርን በእውነተኛ ልብ የማያውቁ/ክፉዎች ሰዎች እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ፈጥኖ እንዴት እንደሚያጠፋቸው ያሳያል። በቁ 18 ላይ የክፉዎችን አጠፋፍ እና አቀጣጥ በሚያዳልጥ መንገድ ላይ ሲሄድ ከሚወድቅ ተጓዥ ጋር ያመሳስለዋል። የሚያዳልጥ ነገር ላይ የቆመ ወይንም የሚሄድ ሰው አወዳደቁ ቅጽበታዊ ነው። እንዲህ አይነቱ ሰው ሳያስበው ራሱን ከመሬት ላይ ወድቆ እንደሚያገኘው ክፉ ሰዎችም እንዲሁ ሳያስቡት የነበራቸው ስኬት ሁሉ ጠፍቶ ራሳቸውን ከተራ ሰው ሁሉ በታች

ሆነው ያገኙታል። ዓይናቸውን ጨፍነው አይናቸውን ሲገልጡ ራሳቸውን የሚያገኙት ሌላ ታሪክ ውስጥ ይሆናል። ይህ የሚሆነው ግን በአጋጣሚ ሳይሆን፣ ይህንን የሚያደርገው እግዚአብሔር ራሱ ነው - እሱ የፍትህ አምላክ ነውና። መዝ 1ን ማንበብ ትችላላችሁ።

ቁ. 19 ላይ የኃጢአተኞች ጥፋት ቅጽበታዊ ብቻ ሳይሆን ድንገተኛ እንደሚሆን ያስረዳል። ነገር ሰላም ነው … ገና ነገን እና ከነገ ወዲያ እንደዚህ እና እንደዚያ እናደርጋለን ሲሉ እግዚአብሔር ግን በድንገት ያጠፉቸዋል። ጉዳዩ ዳዊት በመዝ 37፡35-36 ባለው ክፍል ላይ እንዳለው ነው “ኃጥአን ከፍ ከፍ ብሎ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ለምልሞ አየሁት። ብመለስ ግን አጣሁት፤ ፈለግሁት ቦታውንም አላገኘሁም”። ዘማሪው ዞር ብሎ ሲመለስ እንደ ሊባኖስ ዛፍ ገዝፎ እና ለምልሞ የነበረው ኃጥእ እንደጠፋው እንዲሁ እግዚአብሔርን ባለመፍራት የሚመላለሱት ድንገት ይጠፋሉ።

ቁ.20 ላይ እንደገና በሌላ አይነት መልኩ ኃጢአተኛ እንዴት እንደሚጠፋ ይገልጻል። “ሰው ከሕልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው፣ ጌታ ሆይ አንተም በምትነሳበት ጊዜ፣ እንደ ቅዠት ታደርጋቸዋለህ” (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)። ሕልም ለሚያየው ግለሰብ ሕልሙ እውን እንደሚመስለው ግን ከእንቅልፉ ሲነቃ ያ በሕልም የታየው ነገር ሁሉ እውን ያልነበረ ሆኖ እደሚያገኘው፣ ኃጢአተኞችም እንዲሁ ሲለመለሙና እና ነገር ሲሞላላቸው የእውነት የሚያስፈሩ እና ገናና የሆኑ ቢመስሉም ግን እግዚአብሔር በሚነሳበት ጊዜ ነገራቸው ሁሉ ዜሮ ይሆናል።

ዘማሪው መጀመሪያ ላይ የኃጢአተኞች ገናናነት መንገዳቸውን እንዲከተል ቢፈተንም፣ ግን ወደ እግዚአብሔር ሲጠጋ የተረዳው ነገር የኃጥእ ሕይወት ትርጉም የለሽ እና ፍጻሜ ከንቱ እንደሆነ ነው። ስለዚህም የኃጢአተኛ መንገድም ሆን ስኬት ዋጋ ቢስ ነው። ታዲያ እውነታው እንደዚህ ከሆነ፣ ዘማሪው ከዚህ በኃላ የሚያደርገው ምንድን ነው ብለን ብንጠይቅ ከቁ. 21-28 ባላው ከዚህ በኃላ የሚኖረውን ውሳኔ ይነገረናል።

### መ. በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መልካምነት (መዝ 73፡21-28)

በቀሪው ክፍል ዘማሪው ከላይ ከዘረዘረ እውነት  በመነሳት ከዚህ በኃላ የሚያዋጣም እግዚአብሔርን መሻት እና መከተል እንደሆነ ያስረዳል። ኃጢአተኛ ቢሳካለትም የሚጠፋ ከሆነ፣ ሕይወታቸውን የሚፈትን እና ጻድቅን ለማሰናከል የሚያስጎመጅ ቢመስልም ፍጻሜው እርባና ቢስ ከሆነ ለሰው የሚሻለው ለጊዜው የሚያሳዝን ቢመስልም ለዘለቄታው የሚያዋጣ ስለሆነ እግዚአብሔርን መከተል ነው። ለዚህም ነው ዘማሪው “በሰማይ ካንተ በቀር ማን አለኝ? በምድርም ካንተ ሌላ የምሻው የለኝም” የሚለው (ቁ. 25)። ይህን ሲል በእርግጥ ከላይ እንደዘረዘረ ሰው አይስትም ወይንም አይፈተንም ማለቱ አይደለም - ሰው ምንም ጻድቅ ቢሆን ደካማ ነውና። በኃጢአተኛ ኑሮ ሊቀናም፣ ሊፈተንም ይችላል። ዋናው ነገር ግን ከፈተናው ነቅቶ የሚያዋጣው ጌታን መከትል እንደሆነ መረዳት ነው (ለዚህ ቁ. 26ን በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ያወዳድሩ)።

ይህንን ያስተዋለው ዘማሪ መዝሙሩም የሚደመድመው  ለሰው የሚያዋጣው እግዚአብሔርን በመከተል እና መቅረብ ብቻ እንደሆነ በማሳሰብ ይጨርሳል።  “ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ ጌታ እግዚአብሔርን መጠጊያዬ አድርጌዋለሁ፤ ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ”።

የመወያያ ጥያቄዎች-በሁለት ቀን መወያየት ትችላላችሁ-በርግጥ መሪው እንደሚመራ ይሆናል

1. መዝ 73 ጥናት ዓላማው ምንድ ነው? ከመግቢያስ ሀሳብ ምን ተማራችሁ?
2. የመዝ 73፡1-3 ዋና መልዕክት ምንድ ነው? ልባቸው ለቀና ማለት ምን ማለት ነው?
3. ዘማሪው በሀሳቡ ከእግዚአብሔር መንገድ መሄድ የጀመረው ምን ጊዜ ነው?
4. መዝ 73፡4-12 ዘማሪው ኃጢአተኞችን እንዴት ነው የሚያብራራው? ምን ሆኑ ይላል?
5. መዝ 73፡15-17 ባለው ክፍል ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ሲመጣ እና ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ አገልጋዩ ያገኘውን መልስ ተነጋገሩ።

6. በመዝ 37፡35-36 ከዚህ ክፍል ጋር ምን ይገናኛል?
7. መዝ 73፡ 18-20 ባለው ክፍል አንድ ጊዜ ስኬታማ የነበሩት፣ ለሚመለከታቸው ገናና እና አስፈሪ የነበሩትን እግዚአብሔርን በእውነተኛ ልብ የማያውቁ/ከፉዎች ሰዎች እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ፈጥኖ እንዴት እንደሚያጠፉቸው ያሳያል። ይህን ክፍል በማንበብ ይህንን እውነት ተወያዩ።
8. ዘማሪው ለጥያቄው መልስ ያገኘው መቼ ነው (መዝ 73፡15-17)?
9. **መዝ 73፡21-28 መሠረት ለማንኛውም መንፈሳዊ ጥያቄ መፍቴሔው ምን እንደሆነ ያስተምራል?**
10. **ጌታ ኢየሱስን ዲያብሎስ በሥጋዊ ምኞቶች ሲፈትነው በምን አሸነፈ? (ሉቃስ 4፡1-12) ይህ ምን ያስተምራል?**
11. ዛሬም በእንደዚህ ዓይነት ፈተናዎች የሚያልፉ አማኞች አሉ ብለህ ታስባለህ? አንተስ/ቺስ/ እንደዚህ ዓይነት አማኞች ቢያጋጥሙህ ምን ትመክራለህ?

**መደምደሚያ፡-**

**የክርስቲያን ፈተና ማሸነፊያ መንገድ**

ሁሉም ባይሆኑ በጌታ ላይ በብዙ ድፍረት የሚናገሩና ኃጢአትን እንደ ውሃ የሚጠጡ ኑሮአቸው እጅግ ተሳክቶላቸው ይኖራሉ። በተቃራኒው ደግሞ ፈጹም በጌታ የታመነ ሰው ያልተሳከለት ይመስላል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ አማኞች የኃጢአተኞችን ምድራዊ ስኬት ስያዩ እምነታቸው ሊፈተን ይችላል። መዝሙር 73 ይህንን ፈተና እንዴት ማሸነፍ እንደምንችል ጥበብ ያስተምረናል። ብቻኛውም አማራጭ የሌለው ማሸነፊያ መንገድ በየቀኑ ወደ እግዚአብሔር በእምነትና ጸሎት፣በጌታ ቃል እና በአማኞች ህብረት መቅረብ ነው።

# ጥናት 18

## መዝ 103

## የአምልኮ ጥሪ መዝሙር (ጥሪው ራስንና ሌሎችንም ያጠቃልላል)

**መግቢያ**

ይህ መዝሙር በጥቅሉ የአምልኮ መዝሙር ነው። መዝ 103 እግዚአብሔር ያዳነው ሰው ወይም ህዝብ እርሱን እንዲያወድስ የተደረገ ጥሪ ነው። ዘማሪው እግዚአብሔር ለራሱና ለሕዝቡ ያደረገውን ፍቅርና ምህረት ያስታውሳል። የመዝሙሩ አደረጃጀት ከነጠላ ወደ ብዙ ጥሪ ይሸጋገራል። ማለትም ዘማሪው ራሱ እግዚአብሔርን ለማምለክ ጥሪ ካደረገ በኋላ ህዝቡን ደግሞ ይጠራል። ዘማሪው መዝሙሩን የጀመረውም ይሁን የጨረሰው በዚህ ታላቅ ጥሪ ነው ( "ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ" ቁ.1 እና 22ን ይመልከቱ)። ሙሉ ማንነቱን ጌታን እንዲያመልክ ይጠራል።

መዝ 103፡1-2 እና ከ20-22 የአምልኮ ጥሪ ሲሆን ከ3-5 እግዚአብሔር ለግሉ ነፍስ ያደረገለትን ያስታውሳል። ቁ.6 እና 19 የእግዚአብሔርን አገዛዝ ማለትም ታላቅነቱን በመናገር በተቀሩት ቁጥሮች ግን ለህዝቡ ለእስራኤል እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ምህረትና ይቅርታ ያስታውሳሉ (መዝ 103፡7-18) ። ይህም ከቁ. 7-12 እና 13-18 በመሆን በእኩል በስድስት ቁጥሮች (ሁለትዮሽ ስንኞች-double stanza) ይከፈላል። መዝ 103፡7-12 እግዚአብሔር ለህዝቡ ያደረገለትን በጎነት የሚያመሰግን ሲሆን መዝ 103፡13-18 ደግሞ እግዚአብሔር ታናሽ ለሆነው ህዝብ ያሳየውን ርህራሄና ምህረቱን ያስተምራል። **ጠቅለል ባለ መልኩ** መዝ **19፣24፣ 47፣95፣100፣103፣104፣145 ተመሳሳይ የአምልኮ መዝሙሮች ናቸው።**

**ዓላማ**

**ሙሉ ማንነታችን** እግዚአብሔርን ማምለክ እንዲችል ደጋግመን ራሳችንን በማነሳሳት ሌሎችንም እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ፍቅርና ርህራሄ በማስረዳት እግዚአብሔርን በመሰጠት እንድያመልኩት ጥሪ ማድረግ እንዳለብን ማሳወቅ።

**ሀ. መዝ 103፡1-2 የግል ነፍስ የአምልኮ ጥሪ**

ሌሎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ከመጥራቱ በፊት ዘማሪው መጀመሪያ ሙሉ ማንነቱን (ራሱን) ለአምልኮ ይጠራል። ለዚህም በነጠላ ቁጥር "ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ" ይላል። ይህ እኛንም ተሰጥተን ጌታን እንድናመልክ ያስተምራል። እግዚአብሔር ያደረገለትን ፍቅርና ምህረት ነፍሱ እንድትረሳ አይፈቅድላትም (ቁ..2 "…ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ")። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባወጣ ጊዜ የሚከተለውን ትዕዛዝ ሠጠ "በዚያን ጊዜ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ" (ዘዳ 6፡12)። መርሳት መንገድ ያስለቅቃል።

**ለ. መዝ 103፡3-5 ጌታ እግዚአብሔር ምን ምን እንዳደረገልህ አስታውስ**

የመዝሙሩ ጸሐፊ በዚህ ክፍል እግዚአብሔርን ለማመስገን ስድስት ነገሮችን ያስታውሳል፡- 1. ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ያስባል 2. የእግዚአብሔርን ፈውስ ያስታውሳል 3. ከጥፋት መዳኑን ይናገራል 4. የእግዚአብሔርን የምህረቱንና የቸርነቱን ከለላ ያውጃል 5. አምላክ በሚያስፈልግ ነገር የሚያረካ መሆኑን ያረጋግጣል 6. ሰውነትን የሚያድስ መሆኑንም አረሳም (ኢሳ 40፡31 ይመልከቱ)። እነዚህ ነገሮች አንዱ ከአንዱ ጋር የሚገናኙ ናቸው።

**ሐ. በመዝ 103፡6-12 ከግል ምስጋና ወደ ማህበረሰብ ምስጋና መሸጋገር**

ማህበረሰቡ የሚያመሰግኑበት ምክንያቶች፡-

1. እግዚአብሔር በባህርይ የፍትህ አምላክ ስለሆነ (ቁ.6)። ማንም ሰው ቢበደል ፍርድ በእርሱ ዘንድ አለ። ይህንን ታርክ እስራኤላዊያን ከግብጽ የወጡበት ጊዜ እውነት ያስተምረናል። እግዚአብሔር ፍትህና ፍርድን በፈሪኦን ኃጢአት ላይ አደረገ።
2. ቁ.7-10 ዘማሪው ለእስራኤል በሙሴ በኩል የተገለጠውን ዘላለማዊ ዕቅድ ያስታውሳል። ይህንን ታርክ የዘጸዓት መጽሐፍ ያስተምረናል። ይህም እስራኤል ሳይበድል ቀርቶ ሳይሆን የእግዚአብሔር ምህረቱና ዘላለማዊ እቅዱ እጅግ አስደናቂ ስለሆነ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሰው ጌታ ለኃጢአት ዋጋ ቂጣት የለውም ሳይሆን እያለ ያለው እርሱን ለሚከተልና ለሚያምን ምህረቱን ለሚጠይቅ ጌታ ፍጹም መሃሪ ነው። ይህም ከእርሱ ባህርያት አንዱ ነው። "… እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ" ነው የሚለው። ምህረቱን ለማግኘት እርሱን መፍራት አለብን።
3. መዝ 103፡11-12 ጌታ ለሚፈሩት ኃጢአትን ምን ያህል ከሰው ልጆች እንደሚያርቅ በመናገር ያስተምራል (የሰማይና የምድር ወይም የምስራቅና የምዕራብ ያህል ርቀት)።
4. ህዝቡ በምህረቱ እንደተባረከ ከመዝሙሩ መረዳት እንችላለን። ስለዚህም አምላኩን ማምለክ አለበት።

   *"ካህናቱም በየሥርዓታቸው፥ ሌዋውያኑም ደግሞ። ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ የሚለውን የዳዊትን መዝሙር እየዘመሩ፥ ንጉሡ ዳዊት እግዚአብሔርን ለማመስገን የሠራውን የእግዚአብሔርን የዜማ ዕቃ ይዘው ቆመው ነበር ካህናቱም በፊታቸው መለከት ይነፉ ነበር እስራኤልም ሁሉ ቆመው ነበር" (2 ዜና 7፥6) ።*

   *"ከሕዝቡም ጋር ተማክሮ በሠራዊቱ ፊት የሚሄዱትን፡- ምሕረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ የሚሉትንም፥ ጌጠኛ ልብስም ለብሰው የሚያመሰግኑትን፥ ለእግዚአብሔርም የሚዘምሩትን መዘምራን አቆመ" (2 ዜና 20፥21)። በሌሎች ክፍሎችም መዝሙር መጽሐፍ እንደሚከተለው ያሳል።*
   *መዝ 118፥29 "እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ ቸር ነውና ምሕረቱ ለዘላለም ናትና"።*
   *መዝ 136፥1 "እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና፥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና"።*
   *መዝ 136፥2 "የአማልክትን አምላክ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና"።*
   *መዝ 136፥3 "የጌቶችን ጌታ አመስግኑ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና"*

*መ. መዝ 103፡13-18 እግዚአብሔርና ሰው በዘማሪው መንፈሳዊ ዕውቀት*

**ይህ ታላቅ ምህረት የተሞላ አምላክ ከሰው ልጅ ጋር ስነጻጸር እጅግ የላቀ ነው። ለዚህ ደካማ ሰው የጌታ ምህረት እንዴት እንደበዛ ዘማሪው ያስረግጣል። ይህም ጌታን በታላቅነቱ ለማምለክ ጥሩ ምክንያት ነው። ቁ.13** ላይ በቁ.11 ላይ የተጠቀመውን ሀሳብ ይደግማል ማለትም ምህረቱና ርህራሄው **ለሚፈሩት** (ለንስሃ ራሳቸውን ላዘጋጁ)። ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች አባት ለልጆቹ እንደሚራራ ይራራል። ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች የሰው ልጅ ምንም እንኳን በጊዜ የተወሰነ እንደሆነ ራሱ ጌታ እንደሚያውቅ ዘማሪው ይናገራል። ይህም ከጌታ ዘላለማዊነት ጋር ሰው ስነጻጸር እጅግ ታናሽ ነው። ከ14-18 ባሉት ቁጥሮች ግን ይህ ታላቅ አምላክ ምንም እንኳን ሰው ዘመኑ እንደ ሚጠወልግ ሣር ወይም የዱር አበባ ቢሆንም እርሱን ከፈሩትና ትዕዛዙን ከፈጸሙ ቃል ኪዳኑን ከህዝቡ ጋር ያደርጋል። ጌታ ኢየሱስ በጴጥሮስ የህይወቱ ድካም ምን ያህል እንደታገሰ እናውቃለን። ምህርቱም ፍጹምና ለቁም ነገር የሚያበቃ አምላክ ነው።

### ***ሠ. መዝ 103፡19-22 የመዝሙሩ መደምደሚያ፡- ታላቅ የአምልኮ ጥሪ***

"19 እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች 20 ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።21 ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።22 ፍጥረቶቹ ሁሉ በግዛቱ ስፍራ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ። ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ" (መዝ 103፡19-20) ።

ጌታ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ ነው። የዓለም ሁሉ ገዥ ነው። እግዚአብሔር እንዲመለክ በነዚህ ቁጥሮች ዘማሪው ራሱንም ጭምር አራት ጊዜ ጥሪ ያደርጋል። በብዙ ቁጥር ሶስት ጊዜ ሲጣራ አንድ ጊዜ ግን ራሱን ይጠራል። መደምደሚያው

እንደ መጀመሪያው "ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ" (መዝ 104፡1)በሚለው ጥሪ ነው። (ለዚህ ክፍል ተጨማሪ ማጠናከሪያ እንዲሆን መዝ 48፡1-14) 1. የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ ፡- የዕብራዊያን መልዕክት "የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ" ይላል (ዕብ 1፡6)፣ "እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ" ብሎ ጴጥሮስ ያረጋግጣል (1 ጴጥ 1፡22)፣ "መላእክቱ ሁሉ፥ አመስግኑት ሠራዊቱ ሁሉ፥ አመስግኑት" (148፡1)፣ 2. ቃሉን የሚፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ እንዲባርኩ ይጠራቸዋል"

ቁ.21 3. አገልጋዮች 4. ሰራዊቱ (ህዝብ ሁሉ)፣ 5. በግዛቱ የሚኖሩ (ምድር ሁሉ የጌታ ነው) 6. ፍጥረት ሁሉ (ቁ. 22)።

ጠቅለል ባለ መልኩ ዘማሪው ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ ይጠራል። ሁላችንም የጌታን ታላቁን ምህረት በማሰብ እርሱን ማምለክ አለብን።

**የመወያያ ጥያቄዎች (የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ ትችላላችሁ)**

1. ከመግቢያ ምን ተረዳችሁ?
2. የዚህ መዝሙር ጥናት ዓላማ ምንድ ነው? ለምን ማጥናት ያስፈልጋል?
3. በመዝ 103፡1-2 መስረት ህዝቡን ለአምልኮ ከመጥራቱ በፊት ምን አደረገ? ለምን?
4. የመዝ 103፡1-2 ማሳሰቢያ ምንድ ነው? ከዘዳግም 8፡11-20 ምን ግንኙነት አለው?
5. በመዝ 103፡3-5 ለአምልኮው ምክንያት የሆኑትን ስድስት ነገሮች ተነጋገሩ።
6. ከቁ.7-12 ያላው ሀሳብ ከ1-6 ካሉት ቁጥሮች ይገናኛል? እንዴት?

**ከዚህ በታች የሁለተኛ ቀን ጥያቄዎች ሊሆን ይችላል**

7. እግዚአብሔር በምህረቱ ብዙ ነው ሲንል፤ አማኝ በኃጢአቱ ይቀጥል ማለት ነው? ቁ.11፣13 እና 17-18 ይነበበ
8. መዝ 103፡11-12 ዘማሪው የተጠቀመው ማብራሪያ ምንድ ነው? ለምን?
9. የጴጥሮስና የጌታ ህይወት ከዚህ ክፍል ጥናት እንዴት እንደሚገናኝ ተወያዩ።
10. በመዝ 103፡13-18 ዘማሪው ሰውን ከእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ጋር ማነጻጸር ለምን አስፈለገ?
11. በመዝ 103፡19-22 በመዝሙሩ መደምደሚያ ለአምልኮ ጥሪ የሚያቀርባቸው ለነ ማን ነው?
12. ከዚህ ጥናት ስለራሳችን ህይወት ምን ተማርን?

*መደምደሚያ፡-*

መዝሙር 103 አንድ የእግዚአብሔር ሰው ስለ ኃጢአቱ ምህረት ከአምላኩ ውለታ በማሰብ እርሱም ሁለንተናው አምልኮ እንዲያቀርብ ከራሱ ነፍስ ጋር የሚታገል ሲሆን በተጨማሪም ሌሎችንም የእግዚአብሔርን ታላቁን ምህረትና ይቅርታ እያሰቡ እግዚአብሔርን እንዲያመመልኩ ይጋብዛል። መዝሙሩ እንደሚነግረን ይህን የአምልኮ በረከት የሚያገኙ ጌታን የሚፈሩ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደሆኑም ያስረግጣል። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ባህርይውን ማወቅ ነው። እርሱ ታጋሽና ይቅር ባይ እንደሆነም የፍትህም አምላክ ነው። በአዲስ ኪዳንም በእያንዳንዳችን ህይወት ይህ እውነት እንደሆነም ማናችንም ልንክድ አንችልም። በየቀኑ ስለሚፈሰው ታላቅ ምህረቱ ጌታን በሙሉ ነፍሳችን ልናመልክ ይገባናል።

# ጥናት 19

## መዝሙር 84 (ከጽዮን መዝሙሮች ምድብ)

## መግቢያ

**ጽዮን ( መግቢያው ከመጀመሪያ መጽሐፍ ከጥናት 14 በከፊል ተውስዷል)**

ጽዮን ማለት ምሽግ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ጽዮን የሚል ቃል በተለያየ መልኩ ከ150 ጊዜ በላይ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህ ስም ምድራዊና ሰማያዊ ኢየሩሳሌምን ያመለክታል። ለእግዚአብሔር ሕዝብ መጠሪያም ይሆናል (ኢሳ 40፡1፣ዕብ 12፡22፣ ራዕ 14፡1)። በጥቅሉ የጌታን ህዝብና የእርሱን ከተማ የሚያመለክት ቃል ነው።

**" የቆሬ ልጆች መዝሙር"**

**ከመዝሙሩ መግቢያ**

ማንኛውንም መዝሙር ከማጥናታችን በፊት ስለ መዝሙሩ የምናገኙትን አመልካች ነገሮችን ማየት እንዳለብን ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰ ይህም መዝሙር እንደዚሁ ይሆናል። በርዕሱ "የቆሬ ልጆች" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ከተመረጠው ከያዕቆብ ልጆች አንዱ ከሆነው ከሌዊ ዘር ከቆሬ ወገን የሆኑትን መዘምራንን የሚያመለክት ሲሆን በቅዳሴ ሥርዓት የሚያገለግሉ መዘምራን ናቸው። ንጉስ ዳዊት እንዳደራጃቸውም ይነገራል። ቆሬ የሌዊን ልጅ የቀዓትን (የቆሐትን) ቤተሰብ ይወክላል ( 1ዜና 6፡31-47 መሪው ያብራራ)። አሳፍ ከሌዊ ልጆች የጌርጌሶናዊያን ሲሆን ኤዶታም ደግሞ የመራሬ ወገን ነው (ዘኍ 3፡17-51)። ሌዊ ከያዕቆብ 12ቱ ልጆች አራተኛው ሲሆን እግዚአብሔር ለራሱ አገልግሎትም የለየው መሆኑ ይታወቃል። ይህ መዝሙር ምናልባት ደናግል ሴቶች መዘምራንን በከበሮ እያጀቡ ወደ ቤተ መቅደስ እየተጓዙ የተዘመረ መዝሙር እንደሆነ ይገመታል። መዘምራኑ በጊዜው በነበሩ የሙዚቃ እቃዎች የተደራጁና እጅግ የተቀናጁ ናቸው። የመዘምራኑ አለቃ በመዝሙር ጸጋ የተቀባ ነው።

# መዝ 84

ይህ መዝሙር በጽዮን ቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር ህልዎት መገኘት እንዴት ታላቅ ስለመሆኑ ከሚዘመሩ መዝሙሮች አንዱ ነው። ዘማሪውም በእግዚአብሔር ያለውን መታመን ለመግለጽና ከእርሱም ጋር ህብረት ለማድረግ በማደሪያው (በቤተ መቅደስ) መገኘት ምንኛ ግሩም እንደሆነ ይናገራል። ይህን በረከት የተለማመደ አገልጋይ መሆኑም አይካድም።

ነገር ግን ምናልባትም ዘማሪው በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ቀደመው ለመሄድ ዕድል ያላገኘ እንደሆነም ይታመናል።

መዝሙሩ ወደ ጽዮን (ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ) የሚጓዙ ሰዎች ይዘምሩ ነበር። መጠንቀቅ የምያስፈልገን ነገር ቢኖር ማንኛውንም መዝሙሮች ስናጠና በኋለኛውም ዘመንና አሁንም የሚዘመሩ መዝሙሮች እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም።

ይህ መዝሙር በጥቅሉ እንደተጠቀሰው የጽዮን መዝሙር ሲሆን ከመዝሙር 46፥ 48፥ 76፥ 84፥ 87፥ 122፥ 137 ጋር የሚመደብ መዝሙር ነው።

መዝሙሩ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት **(መዝ 84፡1-4፤5-7 እና 8-11 ናቸው)።**

**ሀ. በእግዚአብሔር ህልውና የመገኘት ናፍቆት መዝ 84፡1-4፤ቁ.10**

ቤተ መቅደስ (በማደሪያው አዳባባይ የመገኘት ናፍቆት)።
ዘማሪው የጌታን ማደሪያዎቹን ሲናፌቅ በሚታይ ህንጻ መገኘቱን ብቻ ማለቱ ሳይሆን ዋናው ናፍቆቱ በእግዚአብሄር መንፈሳዊ ህልዎት/መገኘት መኖር ነው። ዘማሪው በቁ.2 እንደሚጠቅስ ሁለንተናው (ነፍሱ፣ሥጋውና ልቡ) ፈጣሪውን እንደሚናፍቅ ይናገራል (መዝ 42፡1)። በጌታ ፊት ምንም ሀሳብ ሳይከፋፈል በሙሉ ማንነት መገኘት ትልቅ ክብር ነው። እንደዚህ አስበን እናውቃለን? በሙሉ ማንነት እንዳንገኝ ተግዳሮቶቹ ብዙ ናቸው። ቁ. 3 እንደሚነግረን አገልጋዩ በማደሪይዎቹ አከባቢ በምኖሩት ድንቢጦች/ጫጩቶች እንኳን ቀንቷል። ይህ እጅግ የላቀ ናፍቆት ነው። ቁ.4 ላይ በእግዚአብሔር ፊት በመገኘት መባረክ ብቻ ሳይሆን በዚያም ጌታም ለዘላለም መመስገን እንዳለበት ይናገራል። ቁ. 10 ይህንን ናፍቆት ያጠናክራል። መዝ 42፡1-2 ዘማሪው ለጌታ ቤት ያለውን ጥማት ይናገራል፡ (ይነበብ)።
ስለዚህ ማደሪያዎቹ የተወደደና የእግዚአብሔር መገኛ ቦታ ነው። ይህ ደግሞ በቁ. 1 እና 10 መሰረት ማምለጫና መሸሸጊያ ሲሆን በቁ. 2 መሰረት ደግሞ ማምለኪያና ማመስገኛ ቦታ መሆን አለበት። ለዚህ ሁሉ ምክንያት የጌታ መገኘት ብቻ ነው። ለእስራኤል ህዝብ ያለ አምላካቸው ህልዎች ቤተ መቅደሱም ይሁን ታቦቱም ዋጋ አልነበራቸውም።

**ለ. መዝ 84፡5-7 ጉዞ ወደ ህልውና (ወደ ቤተ መቅደስ የመጓዝ ናፍቆት፣ቅንዓት)**

84፡5 እንደሚነግረን አማኝ ልቡ ወደ ማደሪያዎቹ ጉዞ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ያሳስባል። ይህም ደግሞ መባረክ ነው። በረከቶቹም ቁ6 እና 7 ላይ ተጠቅሷል። እነርሱም 1. **በለቅሶ ሸለቆ** (ከዮርዳኖስ ወደ ኢየሩሳሌም በሚወስድ መንገድ ያለ ደረቅ ወይም እርጥብ ቦታ ሆኖ ግን ለተጓዦቹ የማይመች ቦታ ነው። ትምህርቱ መከራ ውስጥ እንኳን ቢሆን ወደ ጌታ ህልዎት ሲኬድ ደስ ይላል ማለት ነው) በዚያ በሚያልፍበት ጊዜ የምንጭ መፈለቂያ ቦታ ያደርግለታል፣ማለትም ብዙ ዝናብ እንደሚወርድ ይሆናል። በታላቅ ችግር ውስጥ እንኳን ቢሆን የእግዚአብሔር ህልውና በረከታቸው ነው (የዮሴፍ ህይወት አስቡ)። 2**. ከኃይል ወደ ኃይል** ይሄዳሉ ማለትም አይወድቁም ምክንያቱም ከሁሉ የበላይ የሆነ የጽዮን አምላክ ህልዎት ከእነርሱ ጋር ነውና ። ስለዚህ የላይኛውን መንገድ ማሰብ የህይወት በረከት ያመጣል።

በአዲስ ኪዳን የያዕቆብ መልእክት በረከት ካላይ እንደሆነ አስረግጦ ይናገራል "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕ 1፥17)። እግዚአብሔር አይለውጥም።

**ሐ. መዝ 84፡8-12 በጌታ መንፈስ መገኘት የጌታን በረከት መካፈልና ከእርሱ ጋር መነጋገር**

በዚህ ህልዎት ለጌታ ጸሎት ማቅረብ ትልቅ በረከት ነው። ስለዚህም ዘማሪው ለጌታ ጸሎት ያቀርባል "የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማ የያዕቆብ አምላክ ሆይ፥ አድምጥ" (መዝ 84፡8)። በዚህ መዝሙር ዘማሪው አራት የተላያዩ ስሞችን እንደ መገለጫ ይጠቀማል (የሠራዊት ጌታ፣ሕያው አምላክ፣ንጉሤም አምላኬም፣ ያዕቆብ አምላክ ናቸው)። እነዚህን ስሞች ማንሳቱ እምነቱን ያጠነክራል። ስም ገላጭ እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። በእርግጥ ይህ ጸሎት ጌታ ለቀባው ለንጉሱም ዘማሪው እየጸለየ እንደሆነ ግልጽ ነው ። ይህ ሲሆን ኢየሩሳሌም የተጠበቀች ስለምትሆን ወደ ኢየሩሳሌም የሚደርግ ጉዞም የሰመረ ይሆናል። ለመሪዎች የመጸለይ ኃላፊነት አለብን። ይህን በአዲስ ኪዳንም እንድናደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ጢሞ 2፡1፣ ሮሜ 13፡1-7)። ይህ ጸሎት ንጉሱ ህዝቡን በፍትህ እንዲያስተዳደርና ሀገሪቱም ሰላም እንድትሆን ያደርጋል። ለዚህ ሁሉ ከምንም በላይ በጌታ መታመን አማራጭ የሌለው ነገር ነው። ስለዚህም ዘማሪው ቁ.9 ላይ በጸሎቱ በጌታ መታመኑን ይገልጻል። ይህ ሀሳብ ቁ.12 ላይም ተደግሞ ይገኛል። በቁ.10 እና ከቁ.1-4 እንደተጠቀሰው በጌታ ቤት መገኘት ከምንም ጋር ሊነጻጸር እንደማይችል ነው። ቁ.11 ሁለት ነገሮችን ይናገራል 1. ጌታ ስለ ምህረቱ ለህዝቡ ጥበቃ ያበዛል ብርሃናቸው፣ኃይላቸውና ሞገሳቸውም ይሆናል ሲሆን 2. ለዚህ ደግሞ ዘማሪው አማኝ ቅን ቢሆን በተጨማሪ በረከት ሊያገኘው እንደሚችልም ይናገራል። ቅንነት በጌታ ቃል እጅግ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ያስተምረናል። አማኝ መልካም ነገር ለማግኘት ቅን መሆን አለበት።

**መ. ወደ ማደሪያዎቹ ጉዞና የአዲስ ኪዳን ትምህርት**

ይህ መዝሙር ወደ የኢየሩሳሌም/ወደ ጽዮን ጉዞ መዝሙር ነው። በአዲስ ኪዳን የአማኞች ህብረት ማድረጊያ ቦታ በግል ከጌታ ጋር ዬትም ቦታ ሲሆን በማህበር ግን ከቅዱሳን ጋር ነው። መገኘቱ መናፈቅና በዚያም በመታመን መጸለይ በግልም በማህበርም ይሆናል። ማደሪያዎቹ ወይም ቤተ መቅደስ ማለት ለመንፈሳዊ ነገር የተለየ ቦታ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ በግልጽ አማኞች ቤተ መቅደስ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" (1 ቆሮ 3፡16)፣ 1 ቆሮ 6፥19-20 "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ"። ስለዚህ ሁል ጊዜ የጌታን ህልውና ውስጥ እንደምንኖር መገንዘብ አለብን። ይህም ብቻ ሳይሆን ጌታን በሥጋችን እንድናመሰግንም ያስገነዝበናል።"10 ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች በኃጥኣን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ፥ በእግዚአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ"። በየዕለቱ በምናደርገው ጸሎት፣የጌታ ቃል ጥናት፣ህብረት በማድረግና በጎ ነገሮችን በማድረግ የጌታን ፊት ማየት ይቻላል።

**የመወያያይ ጥያቄዎች**

1. ይህ መዝሙር የምን መዝሙር ነው? ተመሳሳይ መዝሙሮቹንም ጥቀሱ።
2. መዝ 84፡1-4 መሠረት የዘማሪው ናፍቆቱ ምንድ ነው?
3. መዝ 84፡2-3 ምን ትምህርት ያስተምረናል?
4. መዝ 44፡5-7 ከመዝ 42፡1-2 ጋር ምን ይገናኛል።
5. በዚህ መዝሙር የተጠቀሰው "የለቅሶ ሸለቆ" ምንድ ነው?
6. ዘማሪው መዝ 84፡8 ላይ ለንጉሱ መጸለይ ለምን አስፈለገ?
7. መዝ 84፡11 ከጠቅላላ የመዝሙሩ ሀሳብ ጋር እንዴት ታዩታላችሁ? ይብራራ
8. በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሰው ከቤተ መቅደስ ትምህርት ጋር ምን አንድነት አለው? "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" (1 ቆሮ 3፡16)፣ 1 ቆሮ 6፥19-20 "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ"።

# ጥናት 20

## የጥናት ክፍል መዝ 33፡1-22

### የአምልኮ/የምስጋና መዝሙር (ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ፈጣሪነት የተሰጠ አምልኮና ምስጋና)

*መግቢያ፡-*

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ የመዝሙር ምዕራፍ 33 ጸሐፊ ማን እንደሆነ አልተጠቀሰም፡ ይሁን እንጂ በግሪኩ ቅጂ መዝሙር ምዕራፍ 33 የጻሐፊው ንጉሱ ዳዊት መሆኑ ተገልጾል። ስለዚህ ለዚህ ጥናታችን ምዕራፍ ሰላሳ ሦስትን የጻፈው ንጉሱ ዳዊት መሆኑን በመስማማት ፡ የምንመለከተው ይሆናል። መዝሙር 33ን በውዳሴና በአምልኮ መዝሙር መካከል የሚመድቡት ብዙዎች ሲሆኑ፡ አምልኮውም በፍጥረት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን የእጁን ሥራ በማየት በምስጋናና በአምልኮ ማክበርን ያስተምራል።

እግዚአብሔር በቃሉ ይፈጥራል፣ይናገራል፡ የሚለው ከብሉይ ኪዳን አብይ ትምህርቶች አንዱ ነው። በመደጋገም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚለው አባባል በነቢያት መጽሐፍ ውስጥ እጅግ አዘውትሮ የተጠቀሰ ለመሆኑ የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት በጨረፍታ ብቻ መመልከቱ የሚበቃ ይሆናል። እግዚአብሔርን ከሌሎች አማልክት ተብዬዎች የሚለየው አንዱ እና ዋናው እርሱ በቃሉ የፈጠረ፣የሚናገርና የሚያይም አምላክ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

በአዲስ ኪዳንም ይህንኑ ሃሳብ ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችሁ በነቢያት ተናግሮ፡ ሁሉን ወራሻ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ይላል (ዕብ1፡1)። ዛሬም እግዚአብሔር ለህዝቡ በተቀደሰው ቃሉ በኩል ህያው ድምጹን ያሰማል እሱ ከመናገር ያልተቆጠበ ስለሆነ የሚሰማ ጆሮ ያለው ግን ይስማ የሚለው ማሳሰቢያ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ መደምደሚያ ሆኗል።

ታዲያ እግዚአብሔር የሚፈጥርና የሚናገር አምላክ ብቻ ሳይሆን እርሱ ዓይኖች ያሉት የሚያይም አምላክ እንደሆነ የሚዘነጋ ጉዳይ አደለም።

*መዝሙር 33 ለጥናታችን እንዲመች እንደሚከተለው በመከፋፈል ምዕራፉን ልንመለከተው እንችላለን፡*

***መዝ 33፡1-3 በደስታ የማመስገን/የማምለክ ጥሪ፣***

**ከቁጥር 4-11 ስለ ማመስገን ምክንያት፣,**

**ከቁጥር 12-15 የእግዚአብሔር ባሕርይ፣**

**ከቁጥር 16-19 የሰውን ብርታትና ከንቱነት,**

**በመጨረሻም ከቁጥር 20-22 በእግዚአብሔር ላይ መታመን እና ተጨማሪ የምስጋና ጥሪ።**

የመዝሙሩን የአዘማመሩ ዘይቤ እንደሚከተለው ይሆናል፡- **ዘማሪው** 1-3፣ **መዘምራኑ** ከ4-19 እና **ህዝቡ** ከ20-22 ህዝቡ እንደዘመሩትም ይታመናል። መዝሙሩ በምስጋና/አምልኮ ጥሪ ከፍቶ (1-3) በምስጋና/አምልኮ ጥሪ ይዘጋል (20-22)።

#### *ሀ.* መዝ.33፡1-3 በደስታ የአምልኮ ጥሪ ወይንም ግብዣ

1. ጻድቃን ሆይ፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ለቅኖች ምስጋና ይገባል።
2. እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት፥ አሥር አውታርም ባለው በበገና ዘምሩለት።
3. አዲስ ቅኔም ተቀኙለት፥ በእልልታም መልካም ዝማሬ ዘምሩ

በእነዚህ ቁጥሮች ዳዊት ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ እንዲሰኙ ያመለከትና ደስታቸው እንዴትና በምን መሆን እንዳለበት ይዘረዝራል። በጊዜው በነበሩ የሙዚቃ እቃዎች እንዲያመሰግኑ ይጠይቃሉ። ይህም በየቀኑ በአዳዲስ ቅኔ ጌታ መመለክ እንዳለበት ያሳስባል። ፊል 4፡4 ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ይላል። ደስታችንን በምስጋናና በአምልኮ መግለጥ አለብን።

**ለ. መዝ. 33፡4-12 ለምን በደስታ የማመስገን/የማምለክ ጥሪ አስፈለገ? (ስለ እግዚአብሔር ቃል ህያውነት በተፈጥሮ ውስጥ)4፡የእግዚአብሔር ቃል ቅን ነውና ሥራውም ሁሉ በእምነት ነውና።**

4.የእግዚአብሔር ቃል ቅን ነውና ሥራውም ሁሉ በእምነት ነውና

5. ጽድቅንና ፍርድን ይወድዳል የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች።

6. በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ

7. የባሕርን ውኃ እንደ ረዋት የሚሰበስበው፥ ቀላዮችንም በመዝገቦች የሚያኖራቸው።

8. ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፥ በዓለም የሚኖሩ ሁሉም ከእርሱ የተነዋ ይደንግጡ።

9. እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም።

ዘማሪው በእነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር ቃል ተንኮል ወይንም እንከን የሌለበት ንጹህ መሆኑን እና የሚሰራውም ሁሉ የታመነና ፍትህ የተሞላ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ከአፉ የሚወጣ የእግዚአብሔር ቃል ኃይል፣ ስልጣንና ፍትህ የተሞላ ነው። ስለሆነም ሚዛን የሚጠብቅና የማያዛብ መሆኑን ያስረዳል። ይህንን ከገለጸ በኋላ ከዚህ ከከበረው የእግዚአብሔር ቃል ምድር እንደተሞላች እና በቃሉ ጸንታም እንደቆመች ይናገራል። አያይዞም ከዘፍ 1፡ ጀምሮ እንዴት እግዚአብሔር የሚታየውን እና የማይታዩትን በውስጡ ያሉትንም ሰራዊት ሁሉ ከአፉ በወጣው በህያው ቃሉ ካለመኖር ወደ መኖር እንዳመጣቸው ያስተምራል። ሰማይ ብቻ ሳይሆን ሰማዮች የጸኑት በውስጡም ያሉት ሁሉ የተፈጠረቱት በቃሉ ነው ይለናል። በየብስ ላይ የሚታየውን ባህርን በምድር ከርስም ውስጥ ያለውን ቀላዮችን ገደብና ዳርቻ ያደረገላቸው በቃሉ ከሆነ፡ በቃሉ የተፈጠሩት ፍጥረታቱ ሁሉ **እንግዲያውስ እግዚአብሔርን ሊፈሩት ሊያመልኩትና** ሊያከብሩት እንደሚገባቸው ይናገራል።

**መዝ 33፡10-12 የእግዚአብሔርን ምክንያት**

10፡እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ያጠፋል፥ የአሕዛብንም አሳብ ይመልሳል

11፡የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል። የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው

12፡እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ምስጉን ነው፥ እርሱ ለርስቱ የመረጠው ሕዝብ

የእግዚአብሔር ቃል ፍጥረቱ የተገኘበት ብቻ ሳይሆን ፍጥረቱም ሆኑ ህዝቦች አህዛብምን ጨምሮ የሚዳኙበት በዚሁ በቃሉ መሆኑን ያመለክታል፡ በቁጥር 10-11 ዘማሪው የአህዛብን ምክርና የእግዚአብሔር ምክር በተነጻጻሪነት እያመለከተ እንዴት እግዚአብሔር የአህዛብ ምክር እና ሀሳባቸው የቱንም ያህል መልካም የመሰለ ቢሆን ከምክሩ ጋር የሚጣረዝና ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ከሆነ ምክራቸው ሊጸና እንደማይችልና ከንቱ እንደሆነ ያስረዳል። የእግዚአብሔር ምክር እጅግ የላቀ እና የከበረ ከመሆኑ በላይ፡ ላመኑት ደህንነት የሚሆን የረዥም ጊዜ እቅድ እንደሆነ ያሳያል። ስለዚህም አምልኮ ይገበዋል። በመጨረሻም እንዲህ አይነቱ መልካም ሃሳብ ለሰው ልጆች ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ ያለው እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ህዝብ እንዴት የተባረከ መሆኑን ይገልጻል። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ዘላለማዊ ዕቅድ ያለው አምላክ ነው፡፡ ደግሞ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ከፈሩትና ካከበሩት ለልጅ ልጆቻችን እስከ ትውልዱ ፍጻሜ ድረስ ነው። ጌታ ድንገት አንዴ ሆኗል ምን ይደረግ የሚል አምላክ አይደለም። ስለዚህ በደስታ ሊመለክ ይገበዋል።

**ሐ. መዝ. 33፡13- 19 የእግዚአብሔር ህያው አመራር ለሕዝቡ ዋስትና ነው፣ ስለዚህ ሊመለክና ሊመሰገን ይገበዋል (እግዚአብሔር ሁሉን የሚያይ አምላክ ነው)**

13. እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፥ የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ።

14. ከማደሪያው ቦታ ሆኖ በምድር ወደሚኖሩ ሁሉ ተመለከተ፥

15. እርሱ ብቻውን ልባቸውን የሠራ ሥራቸውንም ሁሉ የሚያስተውል።

16. ንጉስ በሰራዊቱ ብዛት አይድንም ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም።

17. ፈረስም ከንቱ ነው፥ አያድንም በኃይሉም ብዛት አያመልጥም።

18. እነሆ፥ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደሚፈሩት ናቸው፥ በምሕረቱም ወደሚታመኑ፥

19. ነፍሳቸውን ከሞት ያድን ዘንድ፥ በራብም ጊዜ ይመግባቸው ዘንድ።

መዝሙረኛው እዚህ ጋር ሲደረስ ትኩረቱን ከእግዚአብሔር ቃል ፈጣሪነት ወደ አሁንም የማስተዳደር ችሎታው ይመለሳል። በዚህም እርሱ የሚናገር ብቻ ሳይሆን የሚያይም አምላክ እንደሆነ ሲያስረዳ፡ እግዚአብሔር ሁሉን ከሰማይ ሆኖ እንደሚመለከት ይገልጻል። ምንም እንኳን እግዚአብሔር በሰማይ ከፍ ብሎ እና ከብሮ የሚኖር ከሰው ልጆች እጅግ በጣም ታላቅና ልዑል ሆኖ የሚኖር ቢሆንም ከሰማይ ሆኖ ሁሉን በቅርብ ሆኖ እንደሚመለከት ይገልጸዋል። እግዚአብሔር ደግሞ በፍጥረት ውስጥ ገዥና ህያው ሆኖ ሲኖር ጥበቃው ምህረቱና ቸርነቱ መገኘቱም ሁሉ አብሮ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ህዝቡ በግብጽ ባርነት በነበረት ጊዜ ከሰማይ ሆኖ በህዝቡ የሚያልፍበትን መከራ እንደ ተመለከተ ይናገረናል (ዘጸ 3፡7)። እግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን እንደሆነ (መዝ 34፡15) የእግዚአብሔር ዓይኖች በስፍራ ሁሉ እንደ ሆኑ ምሳ 15፡3 እንመለከታለን። "ሰለሞንም ቤተ መቅደሱን ሰርቶ ከፈጸመ በኃላ ባሪያህ ወደዚህ ስፍራ የሚጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ፣ በዚያ ስሜ ይሆናል ወዳልኸው ስፍራ ወደዚህ ቤት ዓይኖችህ ሌሊትና ቀን የተገለጡ ይሁኑ እያለ ሲጸልይ እናያለን" (1 ነገ 8፡29)።

እግዚአብሔር የተወሰኑ ሰዎችን ወይንም ወገኖችን ብቻ ሳይሆን ሁሉም በእይታው ቁጥጥር ስር እንደሆነና ማንም እንደ ማያመልጥ እና አልታይም የሚል ሰው እደሌለ ያስተምረናል። የሰው ልጆችንም የልብ ሃሳብ ስራቸውንም ሆነ ጎዳናቸውን ከርቀት ይመለከታል (መዝ 139፡ 1-12)። ጨለማ ልተሸፍን ፣ሌሊትም ልትጋርድ አትችልም።

እንግዲያውስ ሁሉን ማየት በሚችል አምላክ ፊት የሰው ልጅ ብርታትም ሆነ ከንዱ ከንቱ እንደሆነ ያስገነዝብና ይልቁንም የእግዚአብሔር ዓይኖች እርሱን ወደ ሚፈሩት በምህረቱ በሚታመኑት ላይ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ ሊመሰገን/ሊመለክ ይገበዋል። በቁ. 18-19 እንደሚነግረን በአደጋም ሆነ አስቸጋሪ በምንላቸው ጊዜያትም አይኖቹ ለማዳን እና ለመታደግ ቸርነትን ለማድረግ እንደሆነ ያሳያል። የእግዚአብሔር አይኖቹ በምድር ሁሉ የሰው ልጆችን የሚያዩ ቢሆኑም በስሙ በተጠሩት በቅዱሳኑ እና እርሱን በሚፈሩት ላይ ግን በተለየ እንደሆነ ይህ መዝሙር ያመለክታል።

***መ. መዝ 33፡20-22 ስለዚህ ምን ያስፈልጋል፣ ትምክህትና መጎደድ ያስፈልጋል***

20. ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ ታደርገዋለች፥ ረዳታችንና መጠጊያችን እርሱ ነውና።

21. ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋልና፥ በቅዱስ ስሙም ታምነናልና።

22. አቤቱ፥ ምሕረትህ በላያችን ትሁን፥ በአንተ እንደ ታመንን።

በመጨረሻም መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ፈጣሪነቱን፣ገዥነቱን፣አብሮነቱንና የሚያይ አምላክ፣ እንደሆነ አስትውሎ በዚህ አምላክ ላይ መመካቱን እና መታመኑን ይገልጻል፡፡ አምላኩ ተስፋውና መጠጊያው በመሆኑ ምዕራፉን ሲከፍት ጻድቃን በደስታ እንዲያመልኩት ሲጋብዝ እንዲሁ ያንኑ ሃሳብ መደመደሚያው በማድረግ ክፍሉን እጅግ በጣም ውብ እና ማራኪ በሆነ የምስጋና ጥሪ ይፈጽማል።

**የመወያያ ጥያቄዎች (የሁለት ቀን ጥናት ቢሆን የተሻለ ለመማር ይጠቅማል)**

1.ከመዝ 33 መግቢያ ምን ተረዳችሁ? በአጠቃላይ ይህ መዝሙር ከምን መዝሙሮች ይመደባል?

2.መዝ 33፡1-3 ዘማሪው ያቀረበው ግብዣ ምን አይነት ነው? በዝርዝር ተነጋገሩ? ለምን?

3. በዚህ መዝሙር መሰረት አምልኮን በተመለከት ከክፍሉ ምን ተረዳችሁ? አዲስ ቅኔ ተቀኙለት የሚለውን እንዴት ተረዳችሁት? በየቀኑ አዲስ መዝሙር መጻፍ አለብን? ታዲያ ምንድ ነው?

4. መዝ 33፡.4-9 የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት ባለ መንገድ ነው የገለጸው? በዝርዝር ጊዜ ወስዳችሁ ተነጋገሩበት (አምስት ነገሮች ከጠቀሳችሁ ጥሩ ነው)።

ይህ ክፍል ከዘፍ 1 ጋር ምን ይገናኛል?

5. መዝ 33፡ 8-9 የዘማሪው ጥሪ ለእግዚአብሔር (የዘማሪዎቹ) ምላሽ ምን መሆን አለበት ይላል? ለምን?
6. መዝ 33፡10-12 የእነዚህ ሁለቱ ቁጥሮች ተደጋጋፊነት ምንድ ነው? ምን ያስተምራል?

***<u>የሁለተኛ ቀን ጥናት መወያያ ጥያቄዎች</u>***

7. መዝ 33፡10-12 ዳዊት እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ህዝብ የተባረከ ያለበት ምክንያቱ ምንድነው?
8. መዝ 33፡13-15 ዳዊት ተመለከት, አየ የሚሉትን ቃላት ደጋግሞ የተጠቀመበት ምን ሃሳብ ለመግለጽ ፈልጎ ነው?

9. መዝ 33፡16-17 አስቀድሞ እግዚአብሔር ያያል ካለ በሃላ ለምድነው ስለ ፈረስና ስለ ሰራዊት የተናገረው? ምንስ ማለቱ ነው? ይህ ደግሞ ከማምለክና ከማመስገን ጋር ምን ይገናኛል?
10. መዝ 33፡18-19 ዳዊት በእግዚአብሔር ምህረት ለሚታመኑት ያላቸው ተስፋ ምንድነው ይላል?
11. መዝ 33፡ 20-22 መሰረት እግዚአብሔርን ተስፋ ስለ ማድረግና ስለ መታመን እና መደገፍና ተወያዩበት።
12. መዝ 33፡ 21 ሃስብ ከመግቢያው ሃሳብ ጋር እንዴት ይገናኛል፡ የዳዊትም ሆነ የህዝቡ የደስታ ምክንያት ምንድነው?
13. ከመዝሙር 33 ምን ተማርን?

## መደምደሚያ፡-

መዝሙር 33 የደስታ የአምልኮ ጥሪ ነው። ሰው የሚደሰተው ጌታን በማምለክ ነው። አምልኮ ሁል ጊዜ በደስታ መሆን አለበት። የአምልኮውም ምክንያት የጌታን ባህርይ በማወቅ ሊሆን ይገባል። ጌታ ቅን፣ታማኝ፣እውነተኛና መሃሪ ነው። በተጨማሪም የመፍጠር ችሎታውን በማሰብ በደሰታ ማምለክ አለብን። በእርሱ መታማን በሌሎች ተዋጊ ኃይሎች ከመታመን ይሻላል። ይህ ደግሞ ድል ይሰጠናል። በአዲስ ኪዳን የፊልጵስዩስ መልዕክትም ይህን እውነት ያስተምራል።

# ጥናት 21

## የጥናት ክፍል መዝሙር 13፡1-6
## የግል ለቅሶ ጸሎት
## (የእስከ መቼ ጥያቄ)

***መግቢያ፡-***

*ለዘመናት ሁሉ የጌታ ሰዎች የሚጠቀሙ ቢሆንም ብዙዎች እንደሚያምኑትት ይህ የግል የጸሎት መዝሙር ዳዊትን ንጉስ ሳኦል በተከታታይ ባሳደደ ጊዜ የጸለየው ጸሎት ነው (1ሳሙ 20፡1-3)። ከዚህ ከግሉ ህይወት የጌታ መንፈስ ሊያስተምረን የተደረሰ መዝሙር ነው። ጩኸቴ ለምን አይሰማም የሚል ጥያቄ የብሉይ ኪዳንም ይሁን የአዲስ ኪዳን አማኞች ህይወት ነው። አንዳንዴ ሰው ከሚያልፍበት መከራና ችግር ብዛት የተነሳ ነፍሱ እርዳታ እና እገዛ ፍለጋ ዙሪያውን ማየት አይቀርም። በተለይም እግዚአብሔርን የሚያምን እና ተስፋም የሚያደርግ ሰው በእንዲህ አይነቱ ሰዓት እግዚአብሔር ከጎኑ እንዲቆምለት እና ካለበት ሁኔታም ፈጥኖ እንዲያወጣው ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ እንደተመኘነውና እንደፈለግነው እግዚአብሔር ከተፍ ብሎ አይዞህ ከጎንህ ነኝ በማለት ካለንበት መከራ ወይም ችግር ውስጥ ፈጥኖ የማያወጣን ጊዜ መኖሩ መካድ የሌለበት እውነት ነው።*

*እንዲህ አይነቱ እውነት ደስ የሚያሰኘን ባይሆንም ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ልናልፍበት የግድ የሚሆኑ ጎዳናዎች አሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ጌታ ኢየሱስ በማቴ 26፡39 በመከራው ሰዓት ጥቂት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ አባቴ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን ብሎ ሲማጸን እና ሲጸልይ እንመለከታለን። እንዲህ አይነቱ ስዓት እጅግ በጣም ከባድ እና እምነት ፈታኝ መሆኑ አያጠያይቅም። ከምናልፍበት ሁኔታ የተነሳ እምነታችንን የሚፈትን የጥያቄ ጎርፍ ሊያሰጥመን ነፍሳችንን ማጥለቅለቅ ይጀምራል። አምላኬ በዚህ ሁሉ ውስጥ የት አለ? እስከ መቼ ነው ይሄስ የሚሆነው የሚሉት በነፍሳችን ውስጥ የማያቋርጥ ጩኸት ይሆናል። ለዚህ ተግባራዊ መልስ ማግኘት ለአንደበት ካልሆነ በስተቀር ቀላል አይደለም።*

*በርግጥ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎችም በተመሳሳይ መንገድ ያለፉ መኖራችው ትልቅ መጽናናት ነው። ለምሳሌ መዝ 10፡1 አቤቱ ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራ ጊዜ ለምን ትሰወራለህ? መዝ 22፡1 አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ። መዝ44፡24 ለምንስ ፊትህን ትሰውራለህ? መከራችንና ችግራችንን ለምን ትረሳለህ? መዝ88፡14። አቤቱ ነፍሴን ለምን ትጥላለህ ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ?*

*እግዚአብሔር ለብቻችን የተወን ፊቱን አዙሩ ከእኛ ርቆ የቆመ መስሎ ይታየናል፡ ስለዚህ የነፍሳችን ጩኸት አቤቱ ለምን ተውኸኝ? ፊትህንስ ከእኔ ለምን መለስህ? የሚሉት ናቸው። ደመና ቢጋርደው ጸሐይ የለም ማለት አይደለም። ስሜቶቻችን የጌታን ህልውና የሌለ ቢያስመስሉም ጌታ ግን አለ።* ***እጅግ አስፈላጊ ነገር የሚሆነው ወደ ጌታ በእምነት መቅረብ ብቻ ነው።***

*መዝሙር 13ን በሶስት ክፍለን ልንመለከትው እንችላለን የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ( መዝ13፡1-2) ዘማሪው የሚያነሳቸው የተውከኝ ጥያቄዎች፡ ሲሆን በመቀጠል (መዝ13፡3-4) የዘማሪውን የነፍስ ጩኸት የሚያሳይ ሲሆን በመጨረሻም መዝ 13፡5-6 የዘማሪውን እፎታና ምስጋና እንመለከታለን።*

## የጥናቱ ዓላማ፡-

*ይህ መዝሙር ማስተማር የፈለገው "እስከ መቼ የሚለው" ጥያቄ በውስጣችን ቢኖርም ጌታ በታማኝነት በጊዜው ስለሚመልስ ቢገባንም ባይገባንም በጌታ ፊት መቆየት እጅግ አስፈላጊ ነው እንደሆነ ነው።*

## *ሀ. መዝ 13፡1-2 የዘማሪው የነፍስ ጥያቄዎች*

1፡ አቤቱ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፉትህን ከእኔ ትሰውራለህ?

2፡እስከ መቼ በነፍሴ እመካከራለሁ? ትካዜስ እስከ መቼ ሁልጊዜ ይሆናል? እስከ መቼ ጠላቴ በላዬ ላይ ይጎደዳል?

በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ዘማሪው እግዚአብሔር እንደረሳው እና እንደተወ ፊቱንም እንደሰወረበት በሚመስል ሁኔታ ውስጥ እራሱን እየተመለከተ ለምን ይሄ ሆነብኝ ሳይሆን ጥያቄው በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አምላኬ ትቶኛል ረስቶኛል ፊቱንም ከእኔ ሰውሯል የሚሉ ናቸው። በዚህ ክፍል "እስከ መቼ" የሚል ጩኸት አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። በህይወቱ ይህን ጥያቄ ማሰላሰል እና ማስተናገድ ጀመሯል። የጊዜውን እርዝማኔና የሁኔታዎቹ አለመለወጥ በውስጡ ያስነሱት ጥያቄዎች ናቸው። መቼም ማንም ሰው ቢሆን በተመሳሳያ ሁኔታ ውስጥ እራሱን ቢያገኝ እግዚአብሔር እንደረሳው እና ፊቱን እንዳዞረበት ሆኖ የማይሰማው ሰው ይኖራል ብሎ መገመት ያዳግታል ። የሚገኝ ከሆነም እጅግ መልካም ነው፡፡ በመቀጠል የጥያቄው ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ያለ እግዚአብሔር መገኘት ብቻውን ከነፍሱ ጋር የሚያደረገው ምክክር መቼ ነው ማብቂያውን የሚያገኘው የሚል ሲሆን ከዚህም ጋር አያይዞ የልቡ ጉዳት እና የስሜቱ መነካት ፈውስ የሚያገኝበትን ጊዜ መናፈቁን ያመለክታል። በመጨረሻም እስከ መቼ ነው በመተው እና በመረሳቱ ምክንያቱ ጠላቱ ሀሴት እና ደስታ የሚሆንለት የሚል ነው። ዘማሪውን ያናወጠው ለጥያቄው በቂ መልስ አለማግኘቱ ብቻ ሳይሆን በሚያልፍልበት ሁኔት ውስጥ የእግዚአብሔር አብሮነት ለማየት በመቸገሩ ጭምር ነው። የእግዚአብሔር አብሮነት ከሁኔታዎች የተነሳ ተሸፍኖበታል። በብሉይ ኪዳን ነብዩ ዕንባቆም ይህን ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቃል (ዕንባ 1፡1-4)። ኃጢአትና ኃጢአተኛ እስከ መቼ ነግሶ ይኖራል? ዘማሪው ጌታ የጠራው ቢመስለውም በሁኔታው ግራ ተጋብቷል። ደመና ቢጋርደው ጸሐይ የለም ማለት አይደለም። ስሜቶቻችን የጌታን ህልውና የሌለ ቢያስመስሉም ጌታ ግን አለ። በእምነት መጽናት አማራጭ የለውም።

## ለ. መዝ 13፡3-4 የዘማሪው ተማጽኖት ወይንም ጉትጎታ (የጩኸቱ ዓላማ)

## 3፡አቤቱ አምላኬ እየኝ ስማኝም ጠላቴ፤አሸነፍኩት አንዳይል።
## 4፡የሚያስጨንቁኝም እኔ ብናወጥ ደስ እንዳይላቸው፡ ለሞትም እንዳልተኛ አይኖቼን አብራ።

በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ዘማሪው በቁጥር አንድ ላይ ፊቱን ያዞረበት የሚመስለውን እግዚአብሔርን እንዲያየው እያለፈበት ያለውን ሁኔታ አምላኬ እየኝ በማለት ይማጠናል። እንዲሁም የነፍሱን ጩኸት ሮሮ እና ጸሎቱን አምላኩ እንዲሰማለት ጉትጎታውን ይቀጥላል። ይህ ካልሆነ ግን እግዚአብሔር እንዳላየውና ጸሎቱም እንዳልተሰማ ሰው በሽንፈቱ ጠላቶቹ እንዲደሰቱበት አይፈልግም። ስለዚህ ታሪኩ በሽንፈትና በሞቱ እንዳይደመደም ነገር ግን አዲስ የትንሳኤ ምዕራፍ እንዲያገኝ ይለምናል። እግዚአብሔር ፊቱን ሲያበራለት ለዘማሪው የመነሳት አቅም እና ጉልበት የሚሆንለት ብቻ ሳይሆን ዓይኖቹ ሲከፈቱለት ጨለማው ሲገፈፍ በሚያልፍበት ሁኔት ተሸፍሮ ማየት የተሳነውን የአምላኩን አብሮነት ማየት ይችላል። መዝ 55፡1-6 ለተጨማሪ ማብራሪያ ቢነበብ ጥሩ ይሆናል። በተለይም ዘማሪው ንጉስ ከሆነ የዘማሪው መውደቅ ከእስራኤል ህዝብ መውደቅና መሰደብ ጋር የተያያዘ ነው። ስሜቶቻችን የጌታን ህልውና የሌለ ቢያስመስሉም ጌታ ግን አለ። ስማኝ፣እየኝ፣ዓይኖቼን አብራ መሰረታዊ ጥያቄዎች ናቸው።

**ሐ. መዝ 13፡5-6 በእግዚአብሔር ላይ መታመን እና መደግፍ ለምስጋና ያበቃናል።**
**5 እኔ ግን በቸርነትህ ታመንሁ፥ ልቤም በመድኃኒትህ ደስ ይለዋል።**
**6 የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፥ ለልዑል እግዚአብሔር ስምም እዘምራለሁ።**

ከዚህ ቀደም ባሉት ቁጥሮች ሁኔታዎች ሁሉ የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ያልታየ እና ጸሎቱም እንዳልተሰማለት ሰው ቢሆንም እውነታው ግን ከዚህ ከሚታየው እና እየሆነ ካለው ሁኔታ የተለየ መሆኑን ነው። በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ዘማሪው በአምላኩ ላይ ያለው መታመን እና መደገፉን ያመለክታል። ከእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት የተነሳ ብቻ የነፍሱ ጩኸት፣ ሮሮው እና ጸሎቱም እንደሚሰማለት እርግጠኛ አድርጎታል። ከዚህ ቀድሞ በህይወቱ የተለማመደው እና የተረዳው ይህ የእግዚአብሔር ቸርነት እና ምህረት አሁን ላለበት ሁኔታ መልስ ሆኖለታል። የሁኔታዎች መልክ ባይቀየርም የእግዚአብሔር ሰው ልብ እና አስተሳሰብ ተቀይሯል። በእግዚአብሔር የማዳን ተስፋ ልቡ ሃሴት ማድርግ ችሏል። ግራ በመጋባት የጀመረውን ጸሎት በምስጋናና በእምነት ዝማሬ ይጨርሳል። ማናችንም በእንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ውስጥ ስንገባ በፍጥነት ወደ ጌታ ልባችንን መመለስ መቻል አለብን። የመዝሙር 73 ዘማሪም እንደዚሁ ዓይነት ጥያቄ ቢኖርበትም

በመጨረሻ ወደ ጌታ መቅረብ አማራጭ እንደሌለው ይናገራል "25 በሰማይ ያለኝ ምንድር ነው? በምድርስ ውስጥ ከአንተ ዘንድ ምን እሻለሁ?26 የልቤ አምላክ ሆይ፥ ልቤና ሥጋዬ አለቀ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው።27 እነሆ፥ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና ከአንተ ርቀው የሚያመነዝሩትንም ሁሉ አጠፋኻቸው። 28 ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል መታመኛዬም እግዚአብሔር ነው በጽዮን ልጅ በሮች ምስጋናህን ሁሉ እናገር ዘንድ" (መዝ 73፡25-28)።

## የመወያያ ጥያቄዎች (የሁለት ቀን ጥናት ቢሆን ይመረጣል)

1. ከዚህ መዝሙር መግቢያ ጹሑፍ ምን ተረዳችሁ?
2. መዝ 13፡1 -2 ድረስ የዘማሪው ጩኸት ምንድ ነው? ለምን?
3. ዕንባቆም 1፡1-4 በማንበብ ከመዝ 13፡1-2 ጋር ምን አንድነት እንዳለ ተወያዩ።
4. በእነዚሁ ቁሮች "እስከ መቼ" የሚለው ሃሳብ መደጋገሙ የሚያመለክተው ምንድነው? ስንት ጊዜ ተደጋገመ?
5. ሰው በእግዚአብሔር ፊጽሞ የተረሳ እንደሆነ ሊሰማው የሚችለው ለምንድነው ትላላችሁ? ልባችንንስ ሁል ጊዜ ማመን እንችላለን? ለምን? 1ዮሐ 3፡19-20
6. በአማኝ ላይ እንዴት ባለ ሁኔታ ነው ጠላት በላዩ የሚኳደደው?

***<u>የሁለተኛ ቀን የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

7. መዝ 13፡3-4 ዘማሪው አምላኩን የሚጠይቃቸው ሶስት ጸሎቶችን ጥቀሱ? ለምን አስፈለገ?
8. መዝ 55፡1-6 በማንበብ ተመሳሳይነቱን በማገናዘብ ተወያዩ።
9. በቁ.4 መሰረት መጨነቁ እንዴት ነው ለጠላቶቹ ደስታ ሊሆን የሚችለው ትላላችሁ? በእግዚአብሔር ላይ መታመኑን ቢጥለው ምን ጥቅም ያገኛሉ? ወይም ዓይን መብራት ለምን አስፈለገ?
10. ሁኔታዎች ባይለወጡ እንኳን የሰው አስተያየትና መረዳት መለውጡ ምን ያኸል አስፈላጊ እንደሆነ ተወያዩ?
11. መዝ 13፡5 ሃሳብ እስከ አሁን ከተናገረው ተቃራኒውን ልዩነቱ ምንድ ነው? ይህስ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ምንድነው?
12. መዝ 13፡6 በለቅሶ የጀመረውን ጉዳይ በምንድነው የደመደመው?
13. መዝ 73፡25-27 በማንበብ አንድነታቸውን በማገናዘብ ተወያዩ።
14. ከዚህ መዝሙር ምን ተማራችሁ?
15. በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ለሚያልፉ ሰዎች በጸሎት በጌታ ፊት ጸንተው እና በእርሱ ላይ ተደግፈው ማለፍ የሚችሉበት ጸጋ እንዲበዛላቸው ለጥቂት ጊዜ እንጸልይ።

## መደምደሚያ

"ለምን ተውከኝ ጥያቄ" ጌታ ከእኛ ጋር ያለመኖር ምልክት አይደለም። በክርስቶስ የህይወቱ መከራ ጊዜም ይህ እውነት ነበር። በዚህ መዝሙር እንደ ተመለከትነው ዘማሪው ብቻ ሳይሆን እኛም በህይወታችን ከምናልበት ሁኔት የተነሳ እግዚአብሔር ከእኛ እጅግ በጣም እርቆ የቆመ የሚመስልበት ጊዜ ሊኖር ይችላል ። እግዚአብሔር የሚያየን ሳይሆን ፊቱን ያዞረብን እና የማያየን የሚመስልበት ጊዜያት ሊገጥሙንም ይችላሉ። ከእኛ እንደ ቀደሙት የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እኛም በእግዚአብሔር ላይ ያለን መታመን እና መደገፍ የሚፈተንበት ሰዓት መኖሩ አይቀርም። በመናወጥ እና በመሸነፋችን ሀሴት ሊያደርግ ጠላታችን በጉጉት የሚጠብቅ መሆኑን ሳንዘነጋ በእግዚአብሔር የማዳን ተስፋ ትላንት በህይወታችን ያደረገውን ለዛሬ እምነት እንድሆነን በማሰላሰል ጸንተን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው እና ልናመልከው ይገባል። ሁልጊዜም ጸሎታችንና ምስጋናችን አይለየን።

# ጥናት 22

## መዝሙር 32

## እግዚአብሔር ይቅር ያለው የጌታ ሰው ውለታውን በማሰብ ያቀረበው ምስጋና ወይም ምስክርነት

*መግቢያ*

በርግጥ አንዳንዶች ይህን መዝሙር እንደ መዝ 51 ከንሰሀ መዝሙሮች ምድብ ቢያስቀምጡም፤ሌሎች እንደሚስማሙት ይህ መዝሙር ስለ ኃጢአት ይቅርታ በደስታ የቀረበ ምስጋና ነው ይላሉ። ሁለቱም ግንዛቤዎች እጅግ የተራራቁ አይደሉም። የዘማሪው ንሰሃና ምስጋናም አለበት። እግዚአብሔር ሰውን ሁል ጊዜ ከእርሱ ጋር ቅንና ንጽሁ በሆነ መንገድ በመኖር በተባረከ ህይወት እንዲኖር ይፈልጋል። አማኝ በንሰሃና ስለ ኃጢአቱ ይቅርታ ምስጋና በተሞላ ህይወት በመኖር ለራሱና ለሌሎችም ጭምር በረከት እንዲሆን የጌታ ጥሪ ነው። ነገር ግን የሰው ልጅ በሥጋውና በሰይጣን ፈተዎች በመቸነፍ ይወድቃል። በዚህም ምክንያት አማኝ ጌታ ለፈለገው ዓላማ ሳይውል ሊቀር ወይም ሊዘገይ ይችላል። ቢሆንም ግን አሁንም ዘማሪ/አማኝ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ይቅር ይለዋል፤እርሱ ምህረቱ ብዙ ነውና ይላል። ለዚህም ምስጋና ይገበዋል። ይህን ስንል ደግሞ እግዚአብሔር ኃጢአትን አይቀጣም ብለን ኃጢአትን እንድንለማማድ ይህ ጥናት ትምህርት መስጠቱ አይደለም። ጌታም በምህረቱ በሚዘብቱ ሰዎች ቁጣውም ታላቅ ስለሆነ እጅግ ጥንቃቄ ያስፈልጋል (1ዮሐ 2፡1-5 ይነበብ)። እነዚህ ሁለቱም ትምህርቶች አይጣረሱም (ምህረቱና ቅጣቱ)።

ዓላማ፡- ጌታ መሃሪ ነው። ለታላቅ ምህረቱም ምስጋና ይገበዋል። ይህን በየእለቱ ማሰላሰል አለብን።

1. ቡሩክ ሰው-የበረከት ማብራሪያ (1-2)
2. ያለመናዘዝ ውጤት (3-4)
3. የኑዛዜ ቃልና ሂደት (5)
4. በኑዛዜ የታደሰ መታመንና ውጤት-ለሌሎች ትምህርት (6-7)
5. የአመለካከት ለውጥ (ሰለኑዛዜ) (8-10)
6. ከኑዛዜ የወጣ ሐሴት (11)

## 1. ቡሩክ ሰው-የበረከት ማብራሪያ <u>(1-2) ብሩክ ማን ነው?</u>

- **መተላለፍ (Transgression)**
- **ኃጢያት (Sin)**
- **ኃጢያት (Iniquity)**
- **ሽንገላ (guile)**

ከላይ የተጠቀሱትን ቃላት መተንተንና ማብራራት የዘማሪው ዓላማ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ ለብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸኃፊዎች እውነት ነው። ቢሆንም እኛ በጥያቄና መልስ ጊዜ በተናጥል አንስተን ብንወያይባቸው ይጠቅሙናል።

1) **ይቅር የተባለለት (To be forgiven)**
2) **የተሸፈነለት (to be covered)**
3) **የማይቆጠርበት (imputeth not)**

መተላለፍ (Transgression) በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ማመፅ በመሆኑ ፤ ሕጉ በተላለፈው ላይ የሚያውጀው ኩነኔ ወይም ወንጀለኝነት አለው። እንዲህ ያለውን ኩነኔ ሰው በጥረቱ ከራሱ ላይ ሊያስወግደው የሚችለው አይደለም። ከፍርድ ሊያመልጥ የሚችል ምንም ምክንያት የለውም። ዘማሪውም ሕጉን ተላልፎ በኩነኔ ውስጥ ሆኖ ፤ እግዚአብሔር በይቅርታው ስላሰበው፤ እንዲህ ያለው መታሰብ ለተላላፊው የተገባ ባለመሆኑ ከአምላክ የሆነ በረከት ነው ይለናል። ካገኘው ይቅርታ ባሻገር፤ የሄደበት ክፉ መንገዱና የፈጸመው መተላለፍ ፤ እንደገና በእርሱ ላይ ለክስ እንዳይነሳ ኃጢአቱ የተሸፈነለትና የማይቆጠርበት በመሆኑ ዘማሪው የተባረከ እንደሆነ ይመሰክራል። በጌታ ፊት መቆም እጅግ መባረክ ነው።

በዚህ ክፍል የምናየው መልዕክት ለአዲስ ኪዳን ዋና መሰረት መሆኑን ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንመለከታለን (ኤር.31፡31-34፣ ሮሜ.4 ፤ ኤፌ.2፡8-9፡ ዕብ.9፡15…)።

## 2) ***ያለመናዘዝ ውጤት (መዝ 32፡3-4)***

***"ዝም ባልሁ ጊዜ"*** *ይህ ሀሳብ ዘማሪው ኃጢአቱን ያልተናዘዘበትን ጊዜ ያመለክታል። 2 ሳሙ.11 ላይ እንደምናነበው ዘማሪው (ዳዊት) ያልተናዘዘው መተላለፉን ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን ኃጢአቱን ለመደበቅ ፈልጎና ወስኖ እንደሆነ ይመስላል። ሆኖም እርሱ ወደ ንስሀ ለመምጣት ባልፈለገ መጠን በውስጡ ይፈጠር የነበረ አንድ ችግር እንደነበር ይነገረናል። ጌታን የሚከተል ሰው ኃጢአቱን መሸፈን በቀጠለ ቁጥር ሰላሙንና ደስታውን ያጣል። ማንም ከጌታ ራሱን መሰወር አይችልም ''እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም'' (ዕብ 4፡13)።*

**"መቃተት"** የሚለው ቃል፤ እንደ ከባድ ከአቅም በላይ የሆነን ግፊት ወይም ጫናን ለመቋቋም በሚደረግ ጥረት ውስጥ የሚመጣ **የጣር ድምፅ** ነው። ሰውነትን የጦርነት ሰልፍ ሜዳ ማድረግ ነው። የዘማሪውም መቃተት ከእግዚአብሔር እጅ መከበድ የተነሳ እንደነበረ ይገልፃል። "በቀንና በለሊት እጅህ ከብዳብኛለችና…"

እግዚአብሔር እጁን በዘማሪው ላይ ያከበደው፤ እርሱን ወደ ንስሀ ለማምጣት እንደነበረ ግልፅ ነው። ጥፋቱም የጌታ ሳይሆን የራሱ የዘማሪው ነበር። ሆኖም በዝምታው በቀጠለ ቁጥር የእጁ ክብደት ተጽዕኖ እንዳደረሰበት ለመናገር፤ "አጥንቶቼ ተበላሹ ኃይሌም የበጋ ትኩሳት እንዳለው ሰው ነገር ከውስጤ ተሟጠጠ" በማለት ይገልጽልናል። የጌታ ህብረት ከሌለ ሰው አቅም የለውም። የዘማሪው ዝምታ ማስተዋል ከሌላቸው በልባብና በልጓም ካልተገሩ በቀር ወደ ጌታቸው እንደማይቀርቡት ፈረስና በቅሎ ተነፃፅሮ በቁጥር 9 ላይ እናገኘዋለን። እንደ ፈረስ ወይም በቅሎ በልጓምና ልባብ መመለስ ካባድ ጉዳት ይሆናል። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአታችን እየወቀሰ ወደ ንስሐ ሊያመጣን ይፈልጋል። የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳን እንቢ ብሎ ያለ ንሰሀ መኖር ከፍሬና ከልምላሜ ያጓድለናል። በዘማሪው ሕይወት የሆነው ለትምህርት ይሁንልን። "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም" (1 ዮሐ.1፡8-10)።

### 3. የኑዛዜ ቃልና ሂደት (5)

በእግዚአብሔር እጅ ክብደት የተረታው ዘማሪ በኑዛዜው ይቅርታን ተቀብሎ እናየዋለን። " አስታውቃለሁ … አልሸሸግሁም … አለሁ .." ኑዛዜ ያደረጉትን የኃጥያት ተግባር በዝርዝር መግለጥና ተግባሩ ኃጥያት ነው ብሎ ማውገዝን ያካትታል። ኑዛዜ ህብረት የማደስ መንገድ ነው። አንዳንድ ጊዜ በኑዛዜ ሂደት ውስጥ ሌሎች ወገኖች ማሳተፍ እንዳለብን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ ነው። ይህን እውነታ ዛሬ በሕይወታችን እንዴት ተፈፃሚነት ሊያገኝ እንደሚችል መወያየትና መበረታታት ብንችል መልካም ነው። ለምሳሌ ይቅርታ መጠያየቅ አንዱ ክፍል ነው። በዚህ ጊዜ ሰላማችን ይመለሳል።

### 4. በኑዛዜ የታደሰ መተማመን (6-7)

ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ.4 ላይ እንዳብራራው ጻድቅ የሚለው ኃሳብ የእግዚአብሔር የይቅርታው ውጤት ስለሆኑት እንጂ በሥራቸው ስለ ፀደቁት አይደለም። ዘማሪው የእግዚአብሔርን ምህረት በመቀበሉ ጻድቁ ሲል ራሱንም ጨምሮ እንደሆነ እናውቃለን።

ኃጥያት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሕብረት ስለሚረብሽብን በበደል ውስጥ ሆነን ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ እርግጠኛ መሆን ያቅተናል። ሆኖም በንሰሀ ልንታደስ እርሱ ከእኛ ጋር እንደሆነ ለማየት ስለምንችል መተማመን እንጀምራለን።

ስለዚህ ዘማሪው ከኑዛዜው በኋላ፤ ሲፀልይ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደሚከበው ፤ በመከራም ሰዓት መሸሸጊያ እንደሆነው፤ ደግሞም የድል ሰው ሆኖ የድል ዝማሬን እንደሚሰጠው ይናገራል። ንሰሀ ለደስታ ምክንያት እንደሆነም ቁጥር 7 ይነግረናል። ግለሰብም ይሁን ህብረተሰብ ከጌታ ጋር ካልታረቀ ፊጹም ደስታ አይኖርም። ደስታውንም ሲያገኝ ጌታን ማመስገን አለበት።

### 5. የአመለካከት ለውጥ (ስለ ንሰሃ ወይም ኑዛዜ) (8-10)

ከቁጥር 8-10 ያለውን ሃሳብ ከቁጥር 3-4 ካለው ጋር አዛምደን ብናይ፤ ዘማሪው ስለ ዝምታው የተገሰፀው መሆኑን እናስተውላለን። በቁጥር 9 ላይ ለሌሎች በመናገሩ የራሱን የቀድሞ መንገዱን ያስተዋለና የገመገመ ይመስላል። አሁን በመማር መንገዱን እያስተካከለ በአምላኩ ፊት ለመኖር የተመከረ መሆኑን ይገልፃል። የእግዚአብሔር እጅ ከብዶበት ወደ ኑዛዜ የመጣው ዘማሪ፤ ኑዛዜው ለእኛ እንደ **"ፈረስና በቅሎ"** አትሁኑ ብሎ ይመክረናል። ፈረስና በቅሎ ስለማይታዘዙ በአፋቸው ልጓም እንደሚገባባቸው መሆን እንደሌለብን እንማራለን። "የክፉዎች ዋይታ ብዙ ነው፣ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ግን ምሕረት ይከበዋል"። ዘማሪው የኑዛዜን ሕይወት በእግዚአብሔር መታመን እንደሆነ፤ ተቃራኒው ደግሞ የክፋት መንገድ እንደሆነ ይገልፃል። የዕብራውያን ፀሐፊ በምዕራፍ 3፡13 እንዳስቀመጠው በኃጢአት መታለል እልከኛ የሆነ ልብ እንዳይኖረንና እግዚአብሔር ሲናገር ለመመለስ እንዳይከብደን ልንጠንቀቅ ይገባናል ይላል። ድንዛዜ የሞት ድልድይ ነው። ለዚህ ጥናት ማጠናከሪያ እንዲሆን 1ዮሐ 1፡1-10 እንደገና አንብባችሁ አገናዝቡ።

### 6. 6) ከኑዛዜ የሚወጣ ሐሴት-የምስጋና ጥሪ (11)

"ጻድቃን ሆይ፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ሐሤትም አድርጉ"።

ሰው ጻድቅ ተብሎ ሊጠራ የሚችለው በንሰሀ ከጌታ ጋር ሲታደስ ብቻ ነው። ጌታም ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል። ቁጥር 10 ላይ ኃጢአተኞች መቅሰፍት የሚጠብቃቸው ሲሆን በዚህ ቁጥር ግን በእግዚአብሔር እንዲደሰቱና ሐሴት እንዲያደርጉ ይጋብዛቸዋል። ይህ እውነት ለእኛ ለአዲስ ኪዳን አማኞች ምን ያህል የከበረ ይሆን? እኛም በየቀኑ በጌታ ላይ ባለን እምነት በመታደስ በደስታና በሐሴት መኖር አለብን። ስለ ታላቅ ምህረቱ ጌታን ማመስገን የክርስቲያኖች ተግባር መሆን አለበት። ዘማሪው ቅኔውን በምስጋና ይደመድማል።

የመወያያ ጥይቄዎች

1. ከመግቢያ የተረዳችሁትን ትምህርት አካፍሉ። የዚህ ጥናትስ ዓላማው ምንድ ነው?
2. ይህ መዝ ከየትኛው መዝሙር ጋር ይመሳሰላል? ለምን?
3. መዝ 32፡1-2 ዋና መልዕክቱ ምንድ ነው?
4. <u>መዝ 32፡3-4 ያለመናዘዝ ውጤት ምንድ ነው? በእኛስ ይሆናል? እንዴት?</u>
5. መዝ 32፡5 መሠረት እግዚአብሔር የዘማሪውን የልቡን ኃጢአት የተወለት መቼ ነው? ምን እንማራለን?
6. መዝ 32፡6-7 ከኃጢአት ዕድሳት ውጤቱ ምንድ ነው? 1ዮሐ 1፡1-10 ከዚህ ክፍል ጋር ምን ግንኙነት አለው?
7. መዝ 32፡9 ላይ "ወደ አንተ እንዳይቀርቡ በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጉሙአቸው፥ ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ" ሲል ምን ማለቱ ነው? በዚህ ምን ምክር እንዳለ እንወያይ።
8. መዝ 32፡11 መሠረት የዘማሪው መደምደሚያ ምንድ ነው?
9. የኃጢአት ውድቀት ለገጠመው ሰው ሚዛን የጠበቀ ምክርህ/ሽ ምንድ ነው
10. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን

## መደምደሚያ፡-

መዝሙር 32 አንድ የእግዚአብሔር ሰው ስለ ኃጢአቱ ይቅርታ ከአምላኩ በማግኘቱ ምክንያት የአምላኩን ውለታ በማሰብ በሁለንተናው እግዚአብሔርን በማመስገን የእርሱን ምህረትና ይቅርታ እያሰበ ከፊቱ አለመጥፋትን ያስተምራል። የምህረቱ ታላቅነትና የይቅርታውም ብዛት ለጥቅማችን እንጂ ለጥፋታችን ምክንያት እንዳይሆን መማር አለብን። ደስታና ሀሴት ለማረን ጌታ ማቅረብ ነፍሳችንን ያስደስታል። በምህረት የሚገኝ ደስታ የአዲስ ኪዳን መልዕክት ማዕከል ነው።

# ጥናት 23

## *መዝሙር* 115

## *የቤተ መቅደስ መዝሙር*

***መግቢያ፡-***

*መዝሙር* 115 *እሥራኤላውያን* በአምልኮ *ሥርዓት* ላይ ከሚጠቀሙባቸው *መዝሙሮች* አንዱ ነው። እግዚአብሔር አምላካቸው *ያዳናቸው* አምላክ እንደሆነ *ያስታውሳል*። ይህ ክፍል በጌታ የሚታመኑ ወገኖች ስለሚኖራቸው ድፍረትና ባርኮት ይናገል፤ በአንጻሩም የጣዖታትን ከንቱነት ያሳያል። ዘማሪው በጌታ ማንነት ላይ ያተኮረ ጸሎትንና ምስጋናን የያዘ ነው።

*መዝሙሩ* ሲጀምር "ለእኛ አይደለም" በሚል ሀረግ በጌታ ማንነት ላይ የተመርኮዘ ልመናን ያቀርባል (115:1-2)። በመቀጠል ደግሞ ጌታ በሰማይ በጽኑ ዙፋኑ ላይ እንዳለና ከአህዛብ አማልክት የላቀ መሆኑን በመግለጽ በአንጻሩ የአህዛብ አማልክትና ለእነርሱ የሚቀርብ አምልኮ ከንቱነት ከ3-8 ባለው ክፍል ይናገራል።

የጌታ የሆኑትን በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ ቢደገፉት የማያሳፍር ጌታ እንደሚባርካቸው ያመለክታል። ይህን ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ጌታ ኃይሉንና ችሎቱን እያሰቡ ህያዋን ዛሬም እስከዘላለም ያከብሩታል። ይህ ታላቅ መልእክት ደግሞ ከ9-18 ባለው ክፍል ተጽፏል። ይህ *መዝሙር* ከመዝ 135፡15-21 ጋር በብዙ ይገናኛል።

## የጥናቱ ዓላማ፡-

***ሀ. እግዚአብሔር ለምን ይነሳል?*** (115:1-2)

በእነዚህ ቁጥሮች ህዝቡ ካሉበት ሁኔታ ሊታደጋቸው ወደሚችለው ጌታ ሲጮሁ "ለእኛ አይደለም" ስለማንነትህ ስትል ተነስ የሚሉ ይመስላል። አንደኛ ስለስምህ ስትል፣ ሁለተኛ ማኅሪና እውነተኛ (ታማኝ) ስለሆንክ ምስጋና የሚያመጣን ነገር በመሀከላችን ሥራ ይላሉ [ዘጸ 32:12፤ 34:6-7 ዘኁል. 14:13-15፤ መዝ. 138:2] ። ሰው የጌታን ክብር መሻማት የለበትም።

***ለ. አምላካችን በሰማይ ነው ጣዖታቶች ግን በምድር*** (3-8)

አምላካቸው እግዚአብሔር በአጠገባቸው ካሉት ከአህዛብ አማልክት የሚለይ፣ ታላቅ ጌታና መመለክ ያለበት እንደሆነ ያስተምራል። ማደሪያው በሰማይ መሆኑ በሰው እጅ ከተቀረጹ ጣዖታትን የሚለይ መሆኑና መላቁንም ያሳያል። ጌታ በፈጠረው በሰው ልጅ ስለተሰሩ ከሰማይ አምላክ ጋር ሊነጻጻሩ አይችሉም ። ከሰዎች ከራሳቸው ያንሳሉ። ጌታ ፍጥረትን ፈጥሮአል፣ በእርሱም ላይ ይሰለጥናል፣ ጣዖታት ግን እንደዚህ አይደሉም።

ጣዖታት ውስን በሆነው በሰው እጅ የተሰሩ ስለሆኑ ከበስተጀርባ ሊሰራ ከሚችል የክፉ ኃይል ካልሆነ በስተቀር እነርሱም ከሰሪዎቻቸው ይብስ ውስኖች ብቻም ሳይሆኑ ምንም የማያደርጉ ናቸው (ኢሳ. 40:18-20፣ 44:9-17፣ራዕይ 9:20) ። ሊያደርጉ የሚችሉትን በተመለከተ የሚገርም አገላላጽን ልብ ማለት መልካም ነው፣ እንደሚከተለው ይላል፡- አፍ አላቸው፣ አይናገሩም፣ አይን አላቸው፣ አያዩም …ይላል (5-7)። ይህ አባባል የጣዖታትን ከንቱነት ያመለክታል። አማልክቶቹ ከንቱ ከሆኑ የሚያመልኳቸውም ከንቱነት፣ ያለማስተዋልንና መታወርን ያሳያል (2ነገሥ 17:15፣ ኢሳ 44፡ 9-20፣ ኤር. 2:5፣ ሮሜ 1:21-32)።

***ሐ. በእግዚአብሔር መታመን(መደገፍ) 9-11***

አሕዛብ በአማልክቶቻቸው (ጣዖታትን) ይታመናሉ። ለራሳቸውም ረዳት ፈላጊ ስለሆኑ አማልክት ለሚታማኑባቸውም ድጋፍ አይሆኑም። በህያው እግዚአብሔር የሚታመን የእሥራኤል ቤት፣ የአሮን ቤት፣ ፍርሃ እግዚአብሔር ያለው ሁሉ ከህያውና አቻና ወደር ከሌለው ጌታ ረደኤትንና ድጋፍን የሚቀበሉ መሆናቸው እውን ነው። በሰው እጅ ስለ ተሰራ ጣኦት በ1ኛ ሳሙ እንደሚከተለው ይላል "ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰዱ ከአቤንኤዘርም ወደ አዛጦን ይዘውት መጡ። ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ወስደው ወደ ዳጎን ቤት አገቡት፥ በዳጎንም አጠገብ አኖሩት።በነጋውም የአዛጦን ሰዎች ማለዱ፥ እነሆም፥ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር ዳጎንንም አንሥተው

ወደ ስፍራው መለሱት። በነጋውም ማለዱ፥ እነሆም፥ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር የዳጎንም ራስ እጆቹም ተቈርጠው በመድረኩ ላይ ወድቀው ነበር የዳጎንም ደረት ብቻውን ቀርቶ ነበር። ስለዚህም የዳጎን ካህናት ወደ ዳጎንም ቤት የሚገቡት ሁሉ በአዛጦን ያለውን የዳጎንን መድረክ እስከ ዛሬ ድረስ አይረግጡም" (1ሳሙ 5፡1-5)።

ስለዚህ እውነተኛውን ፈጣሪ የሚያመልኩ የእሥራኤል ቤት፣ የአሮን ቤት እና እግዚአብሔርን የሚፍሩ ሁሉ ይባረካሉ ደግሞም ከከፉና ከፍርድ ይሰወራሉ።

**መ. የእግዚአብሔር ባርኮት 12-15**

እግዚአብሔር የሁሉ የበላይ አምላክ መሁኑ ብቻ ሳይሆን የሚታመኑትን የቃልኪዳን ህዝቡን የማይረሳ፤ ልሚታመኑት ሰውን ሳይለይ በከፉ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ለእርሱ ምስጋና እና ክብርን በሚያመጣ መልኩ የሚባርክ ጌታ ነው። ዘማሪው የኪዳን ህዝብን የእሥራኤልን ቤት እየጠራ የተለዩለትን ካህናት የአሮንን ቤት እና የእርሱ ፍርሃት ያላቸውን ታናሽና ታላቅ የሚባሉን ሁሉ የሚባርክ ጌታ መሆኑን ያስተምራል።

**ሠ. የእግዚአብሔር ችሎትና የህዝቡ ምስጋና** (16-18)

ፍጥረትን ስንምስለከትና ከህዝቡ የሚወጣን ምስጋና ስንሰማ የጌታን ታላቅነትና ክብር ያበስራሉ። የሰማይና ምድር ፈጣሪ ስለሆነ በምንም ነገር የሚወሰን አይደለም። እርሱ ከፍ ባለ ሥፍራ የተቀመጠ ክቡር ጌታ ነው። የአሕዛብ አማልክት በእግዜአብሔር የእጅ ሥራ፣ ቅርጽ ናቸው። በምንም አኳያ ከእርሱ ጋር አይወዳደሩም።

ዘማሪው በቁጥር አንድ ላይ ከተናገረው ጋር የሚመሳሰልን ሀሳብ ጠንከር ባለ መልክ በመዝጊያ ሀሳቡ ላይ ያቀርባል። እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ህይዋን ብቻ ናቸው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. መዝ 115፡1-2 ዘማሪው ጩኸቱን ወደ ጌታ ያቀረበው እንዴት ነው? "ለእኛ አይደለም" የሚለው አባባል ምን ያመለክታል? እነርሱ ወይም እኛም ምንም ኃላፊነት የለብንም ማለት ነው?
   - በማንነቱ ላይ በመመርኮዝ [ስሙን፣ ምህርቱን፣ እውነቱን ምስጋና በተመለከተ ረገድ]
   - የአህዛብን ተግዳሮት በመግለጽ ረገድስ
2. መዝ 115፡3-8፣መዝ 135፡15-21 የአህዛብ አማልክትና የእሥራኤል አምላክ እንዴት ነው የተነጻጸሩት?
   - አድራሻቸው በየት ነው?
   - ማንነታቸውና ምግባራቸው እንዴት ነው የተነጻጸረው?
   - ምን እንማራለን?
3. 1ሳሙ 5፡1-5 ምን ትምህርት ያስተምረናል?
4. የዘማሪው ጥሪ ለእስራኤል፣ ለአሮን ቤት፣ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ምንድን ነው? ከዚህ ምን እንማራለን መዝ 115፡9-12
5. የእነዚህ ጥሪዎች ልዩነትና መመሳሰል ምንድን ነው?
6. የመታዘዛቸው ፍሬ ምንድን ነው?
7. ከዚህ ክፍል የተማርከውን ለቡድንህ አካፍል።

## መደምደሚያ፡- የጌታ ባርኮት በማን ላይ ነው?

መዝ 115 ህዝቡ አምላኩን እንዲባረክ ያነሳሳል። ባርኮቱም የሚገለጸው በጌታ በመታመን ነው። በአሰርቱ ትዕዛዛት እንደሚከተለው ይላል "3 ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። 4 በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። 5 አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም …" ማለትም የአህዛብ አማልክት በእጅ የተቀረጹ ምስሎችና ዋጋ የሌላቸው እንደሆኑ ማመንና ማወቅ መሰረታዊ ነገር ነው። የአህዛብን አማልክት እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው እርግጠኛ መሆን አለብን። ስለዚህ በጌታ

የሚታመኑትን ማበረታታትና ማጠንከርን ይህ መዝሙር ያስተምራል። ጌታ ከሚያመልከው ህዝብ ተለይቶ ከፍ ባለ ሥፍራ ያለ ጌታ፤ የፈቀደውን የሚያደርግ፣ አንዳች የማይከለክለው ብርቱ ልዑል አምላክ ነው።

# ጥናት 24
# የምንባብ ክፍል መዝ 91፥1-16
# የእምነት መዝሙር
# መግቢያ

**ዓላማ፡-**

ፈጹም በጌታ መታመን በዚህ ዓለም በምናያቸውና በማናያቸው ክፉ ነገሮች በዚህ ምድር ወይም ለሚመጣው ዓለም ጌታ እንደሚያድነን ማስተማር።

መዝሙር 91 16 ቁጥሮች ሲኖሩት መዝሙሩ በጌታ ላይ ያለውን እምነት ለመግለጥ የተዘመረ መዝሙር ነው። መዝ 11፥ 16, 23, 62, 63, 91, 121, 124 ከዚህ መዝሙር ጋር ተያይዞ በምሳሌነት የሚጠቀሱ መዝሙሮች ናቸው። በጌታ የሚታመኑ የማይነቃነቅ ብርቱ ዋስትና እንዳላቸውም ያስረግጣል። ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው መዝሙሩን የጌታ ህዝብ እስከ ዛሬም የሚጠቀኑት ቢሆንም የዚህ መዝሙር ጸኃፊ ሙሴ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ይህን መዝሙር ሙሴ እንደጻፈና በሙሴ ህይወትና አገልግሎት የተከሰቱትን ነገሮች እያሰቡና ጌታም እንዴት እንደታደገው እያገናዘቡ ማጥናት ለጥናቱ ትልቅ ዋጋ ይሰጠዋል። መዝሙሩ ከመዝ 90 እና 92 ጋር የመልእክት ግንኙነት አለው። ይህ መዝሙር በተለያየ ፍርሃት ውስጥ ላሉ እምነትን የሚጨምር መዝሙር ነው። በሉቃስ 4:9-11 ጌታ በተፈተነበት ጊዜ ሰይጣን ከዚህ መዝሙር እንደጠቀሰ ይታወቃል። በተጨማሪም ከዚህ መዝሙር ከመሲሁ ህይወት ጋር የሚገናኝ ነገር አለ ብለውም ይስማማሉ።

በዚህ ምድር እየተከሰቱ ያሉትን ነገሮች ስናይ በምንም ነገር እምነት እንዳይኖረን ያደርጋል። የተመሸጉ ሀገሮች ሲመቱ፣የተፈጥሮ አደጋዎች በዝተው ሲታዩ ትምክህት ከጌታ ውጪ ዋጋ እንደሌለው ማወቅ ከባድ አይሆንም። ። ስለዚህ በጌታ ብቻ እምነት ልኖረን ይገባል።

## መዝሙረ ዳዊት 91

## መዝ 91፥1-2

“ በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል። እግዚአብሔርን፡- አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ”።

ከእነዚህ ቁጥሮች ምን እንማራለን?

ሀ. በጌታ መገኛ ቦታ መኖር እውነትኛ ዋስትና ነው። ሙሴ ሁል ጊዜ ጥያቄው

ዘጸአት 33፥15 መሴም ለጌታ ፡- “አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ፥ ከዚህ አታውጣን”።

ዘጸአት33፥16 “በምድርም ፊት ካለው ሕዝብ ሁሉ እኔና ሕዝብህ የተለየን እንሆን ዘንድ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህ፥ እኔና ሕዝብህ በአንተ ዘንድ ሞገስ ማግኘታችን በምን ይታወቃል? አለው”።

## መዝ 91፡3-8

በመታመን ምክንያት አማኝ ከምን ከምን ይድናል? ጌታ እንዴት ይጠብቀዋል?

ሥዕላዊ መግለጫ፡- አንድ አውሬ ወጥመድ እንደተዘረጋበት ቢያውቅ ወደ ወጥመድ አይሄድም ነበር። ወጥመዱ በሚገጥምበት ጊዜ ድንጋጤ ይገጥመዋል። ዘማሪው እርሱን እንደ ወፍ ወይም አውሬ የሚያድኑ ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢያስብም ነገር ግን ሁሉን የሚያይና የሚችል ልዑል ከሚታይና ከማይታይ አጥፊ እቅድ እንደሚያድነው እምነቱን ያውጃል። ከምን? 1. “ እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና”።

2. "በላባዎቹ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል"።

ምሳሌያው ንግግሩ ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትከላከለው ሲሆን ጋሻ ደግሞ በጦር ሜዳ ከውጊያ መከላከልን ያሳያል። ጌታ ከተለያዩ ዓይነት አጥፊዎች ይጠብቃል። በምን? ዘዳ 32፥11 "ንስር ጫጩቶቹን እንደሚያወጣ፥ በእነርሱም ላይ እንደሚሰፍፍ፥ ክንፎቹን ዘርግቶ" ወሰዳቸው፥ በክንፎቹም አዘላቸው"።

3. ከምን ?" ከሌሊት ግርማ፥ በቀን ከሚበርር ፍላጻ፥ 6 በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፥ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም" (መዝ 91፡5-6)። በጌታ ዘንድ የጠላትንና የክፉትን ድብቅ ሴራ የሚሸፍን ጨለማና ሌሊት የለም። ለምሳሌ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤልሳ ዘመን በህዝቡ ላይ አድማ የሚሰሩትን ያጋልጥና ያድናቸው ነበር። በሙሴም ጊዜ የግብጽ ንጉስ ፈሪኦን መሴን ህዝቡን በሌሊት ለማጥፋት ተከትሉ ቢወጣም ጌታ እርሱን አጠፋው (ዘጸ 15፡1፣ 2 ነገስ 6፡15-19)።

ውጤቱ የጠላቶቹን ውድቀት አማኝ በዓይኑ ሊያይ እንደሚችል በእምነት ያውጃል። " በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ ወደ አንተ ግን አይቀርብም። በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፥ የኃጥኣንንም ብድራት ታያለህ" (መዝ 91፡7-8)። ድነታችንን ማንም ምንም መንጠቅ እንደማይችል እምነት እንዲኖረን ጌታ ይፍልጋል። አማኝ ጌታ የፈቀደውን ያህል እድሜ በምድር በእርሱ ጥበቃ ይኖራል። ከሁሉ በላይ ግን የዘላለም ህይወት ወራሽ ነው። ጠላት ይወድቃል።

## መዝ 91፡ 9-16
## የሚያምን ሰው ጽኑ መከላከያ አለው
### ለምን? ምክንያቱም?

1. ልዑሉን መጠጊያ ስላደረገ "አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ ("እግዚአብሔርን መሸሸጊያ፣ ልዑሉንም መጠጊያ አድርገኸዋልና" (መዝ 91፡9 አዲሱ መደበኛ ትርጉም) ።

"10 ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም"። ለዚህ ቁጥር ጥሩ ማብራሪያ የሚሆነው በግብጽ ሀገር የሆነው ታርክ ነው። ጌታ እግዚአብሔር ህዝቡን እንዳይገድል መቅሰፍቱን አሳለፈ (ዘጸ 12፡28-30)። በጌታ ደም ተዋጅተናል።

2. ጌታ ሰውን እንዲጠብቁት መላእክቱን ስላዘዘ

11 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና

ስለዚህ ከመሰናከል ይጠብቃሉ። ለአማኞች ያለው የጌታ ፍቅር እጅግ ታላቅ ነው ምክንያቱም ፍጥረት ሁሉ ለጌታ ክብርና ለሰዎች ጥቅም ተፈጥረዋል።

3. ስለሚጠብቀውና ድል ስለሚሰጠው

ቁጥር 12 እና 14 ከባድ ነገር ከሚመስሉትን ክፉዎች እንኳን ጌታ ይጠብቃል፤ ድልም ይሰጠዋል። ባለማወቅ ከሚገጥሙን ክፉዎችም ጌታ ይጠብቃል። ይህን ቁጥር ኢየሱስ ክርስቶስ በተነ ጊዜ ክፉ ለጠማማ ዓላማው ጠቅሶታል። ማወቅ ያለብን ሰይጣን በጌታ ላይ ያለንን እምነታችንን ለማድከም አንዳንድ ጥቅሶችን ሊጠቀም እንደሚችል ማወቅና መጠንቀቅ አለብን። "እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል። በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ" (መዝ 91፡12-13)።

ቁጥር 14 እንደሚያስረዳ እግዚአብሔር ከዚህ ሁሉ የሚያስጠለው ዘማሪው በጌታ የሚታመን የእርሱን ስም የሚያውቅ ስለሆነ ነው "በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ" (91፡14)።

# መዝ 91፡15-16
## የእምነቱ መጨረሻ ውጤት

"ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ" 91፡15።

ይህ ቁጥር መከራ የለም ሳይሆን የሚናገረው መከራ ውስጥም ከዘማሪው ጋር ጌታ እንደሚሆን ያስተምራል። መከራ ውስጥ ከእኛ ጋር መሆን ብቻ ሳሆን ያድናል፣ ያከብራል። ለዚህ የዮሴፍንና የመርዶክዮስን ታሪክ ማወቅ ጥሩ ማብራሪያ ይሆናል። የክርስቶስም ህይወትና አገልግሎት የላቀ ምሳሌ ነው።

ብዙ እድሜ፦ "ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥ ማዳኔንም አሳየዋለሁ" ይላል 91፡16። ይህ አባባል በምድር ላይ እድሜ መርዘም ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንግስት ለዘላለም መኖርን ያስተምራል። የቱ ይሻላል?

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከዚህ ጥናት ዓላማና መግቢያ ምን ተማራችሁ?
2. መዝ 91ን የጻፈው መሴ ነው ብለን ብንስማማ ከቁ.1-2 ከሙሴ ህይወት ጋር አብሮ ይሄዳል? አዎን/አይደለም። እንዴት ወይም ለምን? ተወያዩ።
3. ዘዳ 32፥11 እና ዘካ 2፡8 ከዚህ ጥናት ጋር ምን ግንኙነት አለው?
4. ከመዝ 91፡3-8 ምን ተረዳችሁ? አንብባችሁ ተወያዩ።
5. መዝ 91፡13 "በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ" ይህ ማለት እባብ ወይም ዘንዶውን እርገጥ ማለት ነው? ካልሆነ ምንድ ነው?
6. መዝ 91፡16 ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥ ማዳኔንም አሳየዋለሁ" ይህ ማለት በምድር የምንኖረው እድሜ ማለት ነው? ካልሆነስ?
7. ይህ መዝሙር ከመዝ 124፡1-8 ጋር ምን ይገናኛል
8. መዝ 91 ላይ የተጠቀሱ ተስፋዎች ስላሉ ዘማሪው ምንም መከራ አይገጥመውም ማለት ነው?
9. ባጠቃላይ ከዚህ መዝሙር ምን ተማራችሁ? የሚያስፈራራህ/ሽ ነገር በህይወትህ (ሽ) አለ? ከዚህ በኋላ ምን ወሰንክ/ሽ? በዚህ ሳምንት ይህን መዝሙር ለአንድ ሰው አንብብለት። ለማን ________________________________

## *መደምደሚያ*

መዝ 91 በብዙ የተወደደ መዝሙር ነው። አማኞችን በጌታ ላይ ፊጹም እንዲደገፉ እምነት የሚጨምር መዝሙር ነው። ዶሮ ጫጩቶቿን ጭልፊት ልትበላ ከመጣች በራሷ ክንፎች ውስጥ ትሸሽጋለች። ራሷን መስዋዕት ታደርጋለች። ዶሮ አቅሟ የተወሰነ ነው። የኛ እረኛ ግን አቅሙን ማንም አይገድበውም።

እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋም መዝ 121፡4 ዓይኖቻችንን ወደተራሮች አንስተን ረዳታችንን ፍለጋ አንደክምም ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን ከሰራው ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ተረድተናል አውቀንማል። እግራችንን ለመናወጥ አይሰጥም እነሆ እግዚአብሔር ይጠብቀናል ይጋርደናል፡፡ ፀሃይ በቀን አያቃጥለንም ጨረቃም በሌሊት፡ እርሱ ከክፉ ሁሉ ይጠብቀናል ነፍሳችንንም ይጠብቃታል፡ ከሌሊት ግርማ በቀን ከሚበርር ፍላጻ በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር አንፈራም በላባዎቹ ይጋርደናል ከክንፎቹ በታች ተማምነን እንቀመጣለን፡፡ ከምናቃቸውና ከማናውቃቸው አጥቂዎች ይጋርደናል። መዝ 46፥2 "ምድር ብትነዋወጥ፥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም"።